ጅማ ዩኒቨርሲቲ

በማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሑፍ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት

ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

# በግጥም ጽህፈትን ማስተማር የጽህፈት ችሎታን ለማዳበር ያለው አስተዋፅኦ (በማና ወረዳ በጶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

አበባ ንጋቱ

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ፋከልቲ የአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ጥቅምት/2016

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

# በግጥም ፅህፈትን ማስተማር የጽህፈት ችሎታን ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ (በማና ወረዳ በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

አበባ ንጋቱ

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ፋከልቲ የአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ማንያለው አባተ (ፒ.ኤች.ዲ)

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል

ሶሻል ሳይንስና ሒዉማኒቲስ ኮሌጅ

ጥቅምት/2017

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ማህበራዊ ሳይንስና ሰብዓዊነት ኮሌጅ

# የኢትዮጵ ያቋንቋ (ዎች) እናስነ-ጽሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት

# ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በግጥም ፅህፈትን ማስተማር የፅህፈት ችሎታን ለማዳበር ያለው አስተዋፅኦ በማና ወረዳ በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፤ በሚል ርዕስ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በአበባ ንጋቱ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና ወጥነት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦተ ፈርሟል፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት

**አማካሪ**________________________________**ፊርማ**______________**ቀን**________________

**የውጭፈታኝ**___________________________**ፊርማ**______________**ቀን**________________

**የውስጥፈታኝ**__________________________**ፊርማ**______________**ቀን**________________

# ማረጋገጫ

በግጥም ፅህፈትን ማስተማር የፅህፈት ችሎታን ለማዳበር ያለው አስተዋፅኦ፤ በሚል ርእስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በማህበረሰብ ሳይንስና ሰብአዊነት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች)ና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋ ለማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል የተጠቀሱና ዋቢ የተደረጉ መሆኑን እንዲሁም ጅማ ዩኒቨርሲቲ የጥናቱ ህጋዊ ባለቤት መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም________________________________________

ፊርማ_______________________________________

ቀን________________________________________

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሞ ነገሮችን ሁሉ አሳክቶ ለዚህ ላበቃኝ ልዑል እግዚአብሄር ምስጋና ይግባው፡፡ ጥናቱን ሲጀምር የመረጥኩትን ርዕስ ከማስተካከል ጀምሮ የሙያ ፍቅራቸውንና የዕውቀት ፍሊጋቸውን በማመልከት ፈጣን ግብረመልስ እየሰጡ ስራዬን ያለምንም መታከትና መሰልቸት በተደጋጋሚ በማየትና በማረም ዕውቀታቸውን፣ ጊዜያቸውን ጉልበታውን ሳይሰስቱ የጎበጠውን እያቃኑ ጥናቱ አሁን የያዘውን ቅርጽ እንዲይዝ በማድረግ ለዚህ ላበቁኝ  አማካሪዬ ለዶክተር ማንያለዉ አባተ ልባዊ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነዉ፡፡እንዲሁም ይህን ጥናት ሳካሄድ ከፍተኛ ድጋፍና ትብብር ያደረጉልኝ የዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና እንዲሁም በጥናቱ ተሳታፊዎች ለነበሩት የዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ላለፍኩበት የትምህርት ጊዜያት ሁሌም ከጎኔ ላልተለዩኝና እና የተለያየ ሀሳብ በመስጠት ለስራዬ መሳካት እገዛ ላደረጉልኝ ለዉድ ባለቤቴ እና ለተከበሩ ወላጆቼ ሁሉ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

ማረጋገጫ ........................................................ 1
ምስጋና ........................................................ i
ማውጫ ........................................................ ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ........................................................ v
አጠቃሎ ........................................................ vi
ምዕራፍ አንድ ........................................................ 1
መግቢያ ........................................................ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................................ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................ 3
1.3. የጥናቱ መላምት ........................................................ 5
1.4. የጥናቱ ዓላማ ........................................................ 6
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................ 6
1.6. የጥናቱ ወሰን ........................................................ 7
1.7. የጥናቱ ውስንነት ........................................................ 7
ምዕራፍ ሁለት ........................................................ 8
ክለሳ ድርሳናት ........................................................ 8
2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........................................................ 8
2.1.1. የግጥም ምንነት ........................................................ 8
2.1.2 የጽህፈት ችሎታ ምንነነት ........................................................ 9
2.1.3 የጽህፈት ችሎታ ትምህርት አስፈላጊነት ........................................................ 11
2.1.4 ጽህፈትን የመፃፍ ብልሃት ........................................................ 11
2.1.5. የመጻፍ ክሂል በአፍ መፍቻ እና በሁተኛ ቋንቋ ትምህርት ........................................................ 13

2.1.6. የጽህፈት ክሂል ችሎታን ማቀድና የማስተማር መርሆች ...... 14
2.1.7. ግጥምን በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ...... 15
2.1.8. የጥናቱ ንድፈ-ሀሳባናዊ ማዕቀፍ ...... 17
2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ...... 18
ምዕራፍ ሶስት ...... 23
የአጠናን ዘዴ ...... 23
3.1. የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ...... 23
3.2. የናሙናዎች አመራረጥ ...... 23
3.2.1. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ ...... 24
3.2.2. የክፍል ደረጃ የናሙና አመራረጥ ...... 24
3.2.3. የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች አመራረጥ ...... 25
3.2.4. የመምህር አመራረጥ ...... 25
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ...... 26
3.4. የማስተማሪያ መሣሪያ አዘገጃጀትና የማስተማር ትግበራ ...... 27
3.4.1. የማስተማሪያ መሣሪያ አዘገጃጀት ...... 27
3.4.2 የመማር ማስተማር ተግባር ...... 27
3.5. የጥናቱ አሰራር ቅደም ተከተል ...... 28
3.6. የመረጃ አተናተን ...... 28
3.7. የጥናቱ ሥነ ምግባራዊ ሁኔታ ...... 30
ምዕራፍ አራት ...... 31
የጥናቱ የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ...... 31
4.1. የጥናቱ የመረጃ ትንተና ...... 31
4.1.1. የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከጥናቱ ትምህርት በፊት ያላቸው የመጻፍ ክሂል.. 31
4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ...... 38

ምዕራፍ አምስት ............................................................................................................ 41
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች ............................................................................ 41
5.1. ማጠቃለያ ............................................................................................................ 41
5.2 መደምደምያ ............................................................................................................ 42
5.3. የመፍትሄ ሐሳብ ............................................................................................................ 43
ዋቢ ጽሑፎች ............................................................................................................ 45
አባሪዎች ............................................................................................................ 49
አባሪ አንድ፤ የመጻፍ ክሒል መመዘኛ ፈተና ............................................................................ 49
አባሪ ሁለት፤ የፈተና ውጤት ............................................................................................................ 51

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ ገጽ

ሰንጠረዥ 4.1፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ........................32

ሰንጠረዥ 4.2፡- የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ነጠላ የናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ........................................................................................................34

ሰንጠረዥ 4.3፡- የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ነጠላ የናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ........................................................................................................35

ሰንጠረዥ 4.4፡- የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ነጻ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ..............................37

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ግጥም ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በኦሮሚያ ክልል፣ በጅማ ዞን፣ በማና ወረዳ፣ በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ከፊል ሙከራዊ ጥናት ተከናውኗል፡፡ ለጥናቱ ያገለገሉት መረጃዎች በፈተና ተሰብስበው ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስትን እና ነጠላ የናሙናዎች ቲ-ቴስትን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ በቅድሚያ የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና ተፈትነው የተገኘው ውጤት በባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ሲተነተን የጉልህነት ደረጃው (P) 0.184 ሲሆን የቲ ዋጋ ደግሞ 1.341 ነው፡፡ በዚህም በሁለቱ ቡድኖች ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት እንደሌለ ተረጋግጧል፡፡ በመቀጥል የጥናቱ ትምህርት ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች ግጥምን በመጠቀም፣ እንዲሁም ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ በቀረቡት ማስተማሪያዎች ለ10 ክፍለ ጊዜ ከተማሩ በኋላ የድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ከድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኘው ውጤት ተወስዶ የመረጃ ትንተና የተደረገ ሲሆን ትንተናው እንዳመለከተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት በጉልህ ይበልጣል፡፡ ከዚህም በመነሳት ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በጉልህ እንደሚያሳድግ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም መሰረት የአማርኛ መምህራን ግጥምን በመጠቀም ተማሪዎቻቸውን እንዲያስተምሩ፣ የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች በመጻሕፍቱ ላይ ግጥሞችን በማካተት በጥቅም ላይ እንዲያውሉ፣ እንዲሁም ሌሎች አጥኚዎች በሌሎች የስነ ጽሑፍ ዘውጎችና በሌሎች ክሂሎች ላይ ተጨማሪ ጥናቶችን እንዲያጠኑ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የመጻፍ ክሂል የጸሐፊውን የተለያዩ ብቃቶች የሚጠይቅና ለቋንቋ ለመዳና ለተግባቦት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያለው ክሂል ነው፡፡ ክሂሉ ለትምህርት በጣም አስፈላጊ ክሂል በመሆኑ ግለሰቦች ሀሳባቸውን ለሌላ አካል ለማስተላለፍ የሚጠቀሙበት ክሂል ነው፡፡ Hyland (2003) እንደሚገልጹት የመጻፍ ክሂል ነጠላ ክሂል ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ሂደቶችን የሚጠይቅ አእምሯዊ ተግባር ነው፡፡ የመጻፍ ክሂል የሚያካትታቸው ሒደቶችም ማቀድ (planning)፣ ማርቀቅ (drafting)፣ መከለስ (revising) እና አርትዖት (editing) ናቸው፡፡ ምሁሩ እንደሚያስረዱት ተማሪዎች ተከታታይነት ያለውና ትርጉም አዘል ጽሑፍ እንዲጽፉ ለማድረግ እነዚህን ሂደቶች ማካተት አለበት፡፡

Flower and Hayes (1981, p. 373) በበኩላቸው አእምሯዊ ሒደት ንድፈ ሀሳብ (cognitive process theory) የተሰኘውን የመጻፍ ተግባር ያስተዋወቁ ሲሆን ንድፈ ሀሳቡ በመጻፍ ተግባር ላይ አእምሯዊ ተግባራት መረዳትን የዘነጋ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ምሁራኑ እንደሚከራከሩት የመጻፍ ተግባር ችግር የመፍታት ተግባር ሲሆን የጸሐፊውን የማቀድ፣ ሀሳብን ወደ ጽሑፍ የመቀየርና ስራቸውን የመከለስ ተግባራትን ይጠይቃል፡፡ ይህ ምልከታ ተማሪዎች ውስብስቡን የመጻፍ ተግባር በቀላሉ እንዲተገብሩ የሚያስችላቸውን በጥልቀት የማሰብና የፈጠራ ችሎታ ማሳደግን የሚጠይቅ ሲሆን ይህንን ለማድረግ የሚችሉ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መምረጥ ከመምህራኑ ይጠበቃል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዘርፉ ምሁራን የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የፈጠራ አቀራረብን በመደገፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ Grainger, Goouch, and Lambirth (2005) እንደሚያስረዱት ግጥምን ጨምሮ የፈጠራ ስራዎችን ለማስተማሪያነት መጠቀም የተማሪዎችን ተሳትፎና ተነሳሽነት ያሳድጋል፡፡ ምሁራኑ እንደሚያስረዱት ግጥም የሚይዛቸው ምት፣ ምሰላና ምስል ከሳችነት ቋንቋውን በመጠቀም ፈጠራን በተላበሰ መልኩ ራሳቸውንና ሀሳባቸውን እንዲገልጹ

እድሉን ይፈጥሩለታል፡፡ ስለሆነም ግጥምን በመጠቀም ማስተማር ተማሪዎች የቋንቋን የመግለጽ አቅም እንዲረዱና ውስብስብ በሆነው የመጻፍ ተግባራቸው እንዲጠቀሙበት ያግዛቸዋል፡፡

Cameron (2003) ግጥም ለቋንቋ ማስተማሪያነት ከፍተኛ አገልግሎት እንዳለው ያስረዳሉ፡ ፡ ምሁሩ እንደሚያብራሩት ግጥም በተመጠነ መንገድ ስሜትን ለመግለጽ የሚጠቅም ሲሆን ይህም ለቋንቋ ችሎታ እድገት ወሳኝ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም ግጥም ተማሪዎች ቋንቋን እንዲሞክሩ፣ የተለያዩ የአጻጻፍ ዘይቤዎች ጋር እንዲተዋወቁና በመጻፍ ተግባራቸው በራሳቸው እንዲተማመኑ የማድረግ አቅም እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ለቃላት ምርጫና ለዓረፍተ ነገሮች አወቃቀር በጥልቀት እንዲያስቡ ግጥም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን በዚህም አጠቃላውን የመጻፍ ብቃት እንደሚያሳድግላቸው Cameron ያስገነዝባሉ፡፡

Elbow (1998) በበኩላቸው ድምጸት የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ ጠቀሜታው ከፍ ያለ እንደሆነ በመጠቆም ግጥም ደግሞ ተማሪዎች ድምጸት እንዲፈልጉና እንዲጠቀሙበት እንደሚያደርጋቸው ያሳስባሉ፡፡ ምሁሩ እንደሚያስረዱት ተማሪዎች በግጥም አማካኝነት ሲማሩ ቋንቋውን ለመጠቀምና የፈጠራ ጽሑፎችን ለመጻፍ ኃላፊነቱን እንዲወስዱ ያደርጋል፡፡ ይህም እውነተኛና ገላጭ የሆነ ጽሑፍ እንዲጽፉ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለሆነም ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን ግላዊ የጽሑፍ ዘይቤ ለማሳደግና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባቦትን እንዲያከናውኑ ያደርጋል፡፡

ግጥምን ከመጻፍ ክሒል ትምህርት ሂደት ጋር በማቀናጀት ማስተማር የተለያዩ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ከላይ የቀረቡት ምሁራን ሀሳቦች ያመለክታሉ፡፡ ሆኖም ግን ከላይ የተገለጹት ጠቀሜታዎች በውል የሚታወቁት ሲሆኑ ግጥም ከዚህም የሰፋ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይታመናል፡፡ ከእነዚህ በውል ከሚታወቁት ጠቀሜታዎች ባሻገር የሚኖሩትን ጠቀሜታዎች በዝርዝር ለመረዳትም ተደጋጋሚ ጥናቶችን ማከናወን ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ግጥም ያሉት ጠቀሜታዎች የተለያዩ ትምህርታዊ ዓውዶችን መሰረት ስለሚያደርግ ነው፡፡

በሌላ በኩል Nabil (2004፡126) Povey (1972: 18)ን ጠቅሰው ስነ ጽሑፍ የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር ያለውን ጠቀሜታ ሲገልፁ ‹‹ስነ ጽሑፍ ስነ ልቦናዊ እውቀትን

የሚያሳድግ በመሆኑ ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ማንበብን፣ መጻፍን፣ ማዳመጥንና መናገርን ለማሰተማር በጣም ጠቃሚ ነው›› ብለዋል፡፡ ከዚህ ሀሳብ መገንዘብ እንደሚቻለው ስነ ጽሁፍ የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር ሁነኛ መሳሪያ ነው፡፡ ምክንያቱም ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች በተዋበ ቋንቋ የሚጻፉ፣ ልብ አንጠልጣይ የሆኑ ታሪኮችን በውስጣቸው የያዙ፣ በሰው ልጆች ልቦና በቀላሉ ታትመው የሚቀሩና አይረሴ ስለሆኑ አንባቢዎች ታሪኩን በቀላሉ ለመረዳትና ይበልጥ ለማንበብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ለማድረግ ያስችላሉ፡፡ በንባባቸውም የተለያዩ የአጻጻፍ ዘዬዎችንና ስልቶችን ይማራሉ፡፡

ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች ክሒሎችን ለማዳበር የማይተካ ሚና እንዳላቸው Aiex (1990) ይገልጻሉ፡፡ Aiex ሀሳባቸውን የገለጹት በአሁኑ ጊዜ የተደረጉ የተለያዩ ጥናቶችን ውጤት ተመርኩዘው ነው፡፡ ምሁሩ እንደገለጹት ስነ ጽሑፍን መሰረት ያደረገ የማስተማር ሂደት በመጻፍና በማንበብ ክሂል የችሎታ ልዩነት ያላቸውን ተማሪዎች በእኩል ደረጃ ለማስተማር እንዲሁም ስኬታማ በሆነ መልኩ ክሂሎቹን ለማዳበር ተመራጭ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች ስነ ጽሑፋዊ ይዘት ቢኖራቸው ተመራጭ እንደሚሆኑ ያሳስባሉ፡፡

Murat (2005) በበኩላቸው ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች የቋንቋ አጠቃቀምን ለማዳበር ፋይዳው ከፍተኛ እንደሆነ ይገለጻሉ፡፡ Murat እንደሚገልፁት ስነ ጽሑፍ እውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም የሚከተል በመሆኑ ተማሪዎች ስነ ጽሑፋዊ ስራዎችን ሲያነቡ የቃላትን ትርጉም፣ የቋንቋውን ስነ ልሳናዊ መዋቅር፣ የቋንቋውን ተናጋሪዎች የአነጋገር ስርአት እንዲረዱ ያደርጋል፡፡ በተመሳሳይ Hanna (2016) እንደሚያሳስቡት ስነ ጽሑፍ በቋንቋ የበለፀገ በመሆኑ የተማሪዎችን የቃላት ዕውቀትና የቃላት አጠቃቀም ያሳድጋል፡፡ ይህም ተማሪዎች ፅሁፉ ከቀረበበት ቋንቋ ጋር እንዲተዋወቁ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ጽሑፉን በሚያነቡ ጊዜ የቃላትን የተለያዩ ትርጉሞች፣ እንዲሁም አውዳዊ ፍቻቸውን እንዲረዱ በማድረግ የጽሑፉን መልዕክት እንዲገነዘቡ እንደሚያግዛቸውና ይህም በመጻፍ ክሒል ትምህርትና ልምምዳቸው ላይ በጎ አሻራ እንደሚያሳድር ያስረዳሉ፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የተማሪዎች የመጻፍ ክሒል መዳበር በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑም ሆነ ለአጠቃላይ ሕይወታቸው አስፈላጊ ክሒል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ለዚህም ሲባል በቋንቋ

ትምህርት ውስጥ ከተካተቱ ይዘቶች መካከል አንዱና ዋናው ሆኖ በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሑፍ ለመግለጽ ይቸገራሉ፡፡ አጥኚዋ በነበራት የአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ልምድ እንዳስተዋለችው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚቀርቡት የመጻፍ ክሒል ትምህርት ሒደቶች ለመሳተፍም ሆነ የሚሰጧቸውን ተግባራት ለማከናወን ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ ባዬ (1987) እና ተስፋዬ (1981) እንደሚገልጹት የተማሪዎች የመጻፍ ክሒል ችግር በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ከሚማሩ ተማሪዎችም አልፎ እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ድረስ የዘለቀ ነው፡፡

የተማሪዎች የመጻፍ ክሒል ችግር በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት ሲችል ከምክንያቶቹ ውስጥ ውጤታማ የማስተማሪያ ዘዴዎችን አለመጠቀም አንዱ ነው፡፡ ይህንን ተከትሎም የተለያዩ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን የመጻፍ ክሒል ለማሳደግ ያላቸውን አስተዋጽዖ መመርመር ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ጥናቶች በተለያዩ ጊዜዎች ተከናውነዋል፡፡ Nattall (1987) እና Hedge (1987) እንደሚገልጹት እንደ ግጥም የመሳሰሉት ስነ ጽሑፋዊ ስራዎችን በቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም የተማሪዎችን የቋንቋ ብቃት ለማሳደግ ጠቀሜታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በሀገር ውስጥ ከተሰሩ ጥናቶች ውስጥ በገሊላ (2010)፣ ታዛነህ (2012) እና ፍሬሕይወት (2013) ይገኙበታል፡፡ ሶስቱም ጥናቶች ትኩረታቸውን ያደረጉት ስነ ጽሑፍ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ የመረመሩ ጥናቶች ናቸው፡፡ ጥናቶቹ እንዳረጋገጡትም ስነ ጽሑፍን በቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ላቅ ያለ ጠቀሜታ አለው፡፡

ከላይ የተገለጹት ጥናቶች ትኩረት ያደረጉት ስነ ጽሑፍን በቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ላይ ቢሆንም ጥናቶቹ ክፍተት ይስተዋልባቸዋል፡፡ ዋናው የጥናቶቹ ክፍተት ከስነ ጽሑፍ ዘውጎች ውስጥ አንዱን በመጠቀም የሞከሩ ሳይሆኑ ስነ ጽሑፍን በጥቅል የሞከሩ ጥናቶች መሆናቸው ነው፡፡ ይህም ማለት በጥናቶቹ የተገኘው በጎ ውጤት የተገኘው ከየትኛው የስነ ጽሑፍ ዘርፍ ላይ እንደሆነ ያላረጋገጡ ጥናቶች መሆናቸው ድምዳሜያቸውን ያልተሟላ አድርጎታል፡፡ ሌላው የጥናቶቹ ክፍተትም ጥናቶቹ በሙከራ ያረጋገጡት የአንብቦ መረዳት ችሎታን ብቻ መሆኑ ነው፡፡

በአንጻሩ ይህ ጥናት ከላይ የተገለጹትን ሁለት ክፍተቶች ለመሙላት የተከናወነ ጥናት ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍተት ከስነ ጽሑፍ ዘውጎች ውስጥ ግጥምን ብቻ ነጥሎ መሞከር መቻሉ ሲሆን በዚህም የስነ ጽሑፍ ዘውጎች በተናጠል ያላቸው ሚና እንዲታወቅ ይህ

ጥናት አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡ ሌላው ክፍተት ደግሞ ቀደም ሲል በቀረቡት ጥናቶች የመጻፍ ክሂል አለመካተቱ ሲሆን በዚህ ጥናት ስለተካተተ ከቋንቋ ክሂሎች አንጻር የጥናቶቹ ውጤት ሰፊ ዓውድ እንዲኖረው አስችሏል፡፡

በአጠቃላይ አጥኚዋ ባሳለፈቻቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ልምድ እንዳስተዋለችው አብዛኞዎቹ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂላቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህም በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር ሲችል አንዱ ምክንያት የማስተማሪያ ዘዴዎች ውጤታማ አለመሆን እንደሆነ ከላይ የቀረቡት ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም የተማሪዎቹን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ በምን መልኩና በምን አይነት ማስተማሪያዎች መማር እንዳለባቸው በጥናት ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ይህንን ተከትሎ አጥኚዋ ባደረገችው የጥናቶች ቅኝት እንዳረጋገጠችው ትኩረታቸውን ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች ላይ ያደረጉ የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ጥናቶች አጋጥመዋታል፡፡ ይሁን እንጂ በሀገር ውስጥ የተሰሩት ጥናቶች ትኩረታቸውን ያደረጉት በጥቅሉ ስነ ጽሑፍ ላይ እንጂ እንደ ግጥም የመሳሰሉትን የስነ ጽሑፍ ዘውጎች ነጥለው አለመመርመራቸው አንዱ ክፍተት ሆኖ አግኝታዋለች፡፡ እንዲሁም ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ ያላቸውን ፋይዳ የመረመሩ የሀገር ውስጥ ጥናቶች አለማግኘቷም ሌላኛው የጥናቶቹ ክፍተት ነው፡፡ በእነዚህ አነሳሽነት በተከናወነው በዚህ ጥናትም ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ተችሏል፡፡

- ✓ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት ተፈጥሯል?
- ✓ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት ተፈጥሯል?
- ✓ ግጥም ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ምን አስተዋጽዖ አለው?

## 1.3. የጥናቱ መላምት

ይህ ጥናት የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ በመሪነት ያገለገሉ ሁለት መላምቶች ተሰንዝረው ከጥናቱ በኋላ አንዱ ውድቅ ሲደረግ ሌላኛው ደግሞ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

- ✓ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በጉልህ አያሳድግም (አልቦ መላምት)፤
- ✓ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በጉልህ ያሳድጋል (አማራጭ መላምት)፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ ይህ ዓቢይ ዓላማም ሶስት ዝርዝር ዓላማዎችን ያካተተ ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ፤
- ✓ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ፤
- ✓ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መፈተሽ፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ግጥምን በቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስም ፍትነት መሰል ከፊል ሙከራዊ ጥናት የተከናወነ ሲሆን ከጥናቱ የተገኘው ውጤትም ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ለማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘጋጆች እና ለሌሎች አጥኚዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

- ✓ ከጥናቱ የተገኘውን ውጤት በመመርኮዝ አስተያየት ከተሰጣቸው አካላት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይገኙበታል፡፡ የተሰጡትን አስተያየቶች መምህራኑ በግብዓትነት በመውሰድ እንደሚጠቀሙባቸው አጥኚዋ ታምናለች፡፡ ስለሆነም መምህራኑ በዚህ ጥናት ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

- ✓ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን የሚያዘጋጁ ግለሰቦች ይህንን ጥናት በግብዓትነት ተጠቅመው መሳሪያዎቹን እንደሚያዘጋጁና በዚህም ውጤታማ እንደሚሆኑ አጥኚዋ ታምናለች፡፡
- ✓ በመጨረሻም ሌሎች አጥኚዎች የዚህን ጥናት ውጤት በመነሻ ሀሳብነትና በመረጃ ምንጭነት እንደሚጠቀሙበት አጥኚዋ ታምናለች፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተከናወነው በኦሮሚያ ክልል፣ በጅማ ዞን፣ በማና ወረዳ፣ በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ የተገኘው ውጤት ከዚህ ትምህርት ቤት ውጭ የሚገኙ ቦታዎችን ውጤት ላይወክል ይችላል፡፡ ከተጠኚ ተማሪዎች አንጻር በትምህርት ቤቱ በ2016 የትምህርት ዘመን በ9ኛ ክፍል በመማር ላይ የነበሩ የሁለት ምድብ ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ጥናት ሲሆን ከእነዚህ ተማሪዎች ውጭ በሌሎች የክፍል ደረጃዎችም ሆነ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎችን አላካተተም፡፡ ከጥናት ርዕሰ ጉዳይ አንጻር ደግሞ የጥናቱ ርኩረት በመጻፍ ክሂልና ግጥምን በማስተማሪያነት መጠቀም ላይ ብቻ ሲሆን ሌሎች ክሂሎችም ሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎች በጥናቱ አልተካተቱም፡፡ በዚህም መሰረት ይህ ጥናት በተጠቀሰው ትምህርት ቤት በ2016 ዓ.ም በ9ኛ ክፍል በመማር ላይ የነበሩ ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ ለመመርመር የተከናወነ ጥናት ሲሆን ከእነዚህ ጉዳዮች ውጭ የትኛውም ጉዳይ በጥናቱ አልተካተቱም፡፡

## 1.7. የጥናቱ ውስንነት

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህ ጥናት ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ የተከናወነ ጥናት ነው፡፡ ለዚህም በተመረጠው ትምህርት ቤት ከሚገኙ ተማሪዎች ውስጥ ሁለቱን የ9ኛ ክፍል ምድቦች በመምረጥ ከፊል ሙከራዊ ጥናት ተከናውኗል፡፡ ምንም እንኳን የግጥም ውጤታማነት በእውነተኛው የመማሪያ ክፍል ዓውድ የተከናወነ ቢሆንም ጥናቱ ያካተታቸው ሁለት ምድቦች ሁሉንም ተማሪዎች ላይወክል ይችላል፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናት ውጤት የወካይነት ችግር ሊኖርበት ይችላል፡፡ ይህንን ውስንነት ለመቅረፍም ተደጋጋሚ ጥናት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1. የግጥም ምንነት

ስነ ግጥም በእጅጉ ጥንታዊነት እንዳለው የሚነገርለት የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው (ዘሪሁን 1992)፡፡ የሰው ልጅ ለብዙ ዘመናት ሀዘናቸውን ምኞት ፍላጎታቸን የአኗኗር ሁኔታቸውን ልዩ ልዩ ገጠመኞቻቸውን በፅሁፍ መግለፅ ከመጀመራቸው በፊት ስነ ግጥም በቃል ሲባል የኖረ እጅግ የቆየ ኪነጥበብ መሆኑ በስፋት ይነገራል፡፡

ይህ የስነፅሁፍ ዘር በኪነ ጥበብ ዘመነ ታሪክ ብዙ የኖረ በመሆኑ እንደየዘመኑ አዋቂው ከተለያየ እና ኪነ ጥበብ ዝንባሌ የተለያ ብያኔዎችን ሲሰጡት ቆይተዋል፡፡ ከዚህም ተነሳ ሁሉን አቀፍ የሆነ አንድ ወጥ ብያኔው ይህ ነው ብለው ለመጥራት ቀላል አይሆንም፡፡ ግጥም የሕይወት አይነተኛ ምሳሌ በእውነት የሚገለፅበት ነው በግጥም በልበወለድ መካከል አንድ አብይ ልዩነቶች አሉ፡፡ እነሱም የልበወለድ ታሪክ ከጊዜ ቦታ አጋጣሚና ምክንያት ከውጤት ውጪ ግንኙነት የሌላቸው ነገሮች ድርድር ሲሆን ግጥም ግን ሊለወጥ በሚያስችሉ የሰው ልጅ ባህሪያት መልኮዎች መሠረት ድርጊቶችን የሚፈጥር ነው፡፡ ግጥም በጣም ምርጥና በሳል አዕምሮዎችን የሚያፈልቁ ምርጥ አጋጣሚዎች ዘገባ ነው፡፡ ስለዚህ በዓለም ውስጥ ውብና የተሸለ ነው የሚባለው ሁሉ ህያው ያደርጋል (Coil 2007)፡፡ ግጥም የፅህፈት አንዱ ዘርፍ ሲሆን ስሜትንና ሀሳብን ስልትን ዘመን እንዲሁም በተስተካከለ አካሄድ የሚቀናበርበት የአጻጻፍ አይነት ነው፡፡ ግጥም ገጣሚውን ውስጣዊ ስሜት እምቅ በሆኑ ቃላት የሚገልፅበት ሃሳብ ምጥቀት የቋንቋ ውበት እንዲሁም ሙዚቃዊ ቃና ያለው በአብዛኛው መልኩ ስሜት ቅርብ በሆነ ሁኔታ ሀሳብና እምነት ፍላጎት አመለካከት በውብ ቃላት የሚቀርብበት ከዚው በተለየ መልኩ የቁጥብ ቃላት ስነፅሁፍ ነው (Arleis 2005)፡፡

ስነ ግጥም አንድን ነገር ወይም ድርጊት አምቆና አጉልቶ የሚያሳይ ሀሳብ አክርሮና አግዝፎ የሚያቀርብ ችሎታ ያለው በጥቂት ምርጥ ቃላት ብዙ ነገሮችን አምቆ የሚይዝና ሙዚቃዊ ቃናው የስሜት ህዋሳትን በቶሎ የሚነካ ለስሜት ቅበርነት ያለው ስነ ጥበብ ነው:: በዙሪያው (1992 ፣ 126) ኀሳዬ ገብረ መድህን (1965 ፣ 5)ን ጠቅሰው እንደገለፀት በቃሉ ውበትና በስሜት የሚጥም ባለስልትና ባለድንጋጌ የቋንቋ አደራደር ሁሉ ስነ ግጥም ይባላል፡፡ መሳጭነት ያለው ጥበባዊ ግብ መቺነት በአደራደርና ስሜት መሳጭነት የላቀ ጥበባዊ ግብ መቼትነት በአንድ ጎኑ ከቁጥብነትና ከእምቅነት ባህሪው ተነሳ መሆኑም ግልፅ ነው፡፡

ከላይ ስለ ግጥም ምንነት የተሰጡት ብያኔዎች ሁሉም ግጥም የራሱ ባህሪ እንዳለው የሚገልጹ ናቸው፡፡ ግጥም በጥቂት ቃላት ብዙ ማለት የሚቻል ስነፅሁፍ ቅርፅ መሆኑንና ግጥም ሀሳብን ስልትን ዜማን እንዲሁም ምትን በተለያየ ሁኔታ የሚቀርብበት የአፃፃፍ ዓይነት መሆኑ ሃሳብን እና ድርጊቶችን አድምቆ እና አጉልቶ የማሳየት አቅም ያለው በጥቂት ቃላት ብዙ ማለት ሚችል የስነፅሁፍ ቅርፅ በመሆኑ በጥልቀት ያሳያል፡፡ ይህ ማለት ግጥም በዝርው ከቀረበ ፅሑፍ ይበልጥ በአካባቢው ደስታና ማነሳሳት ስሜት የሚፈጥር በመሆኑ አጫጭር ግጥሞችን በመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ አውድ አቅርቦ ማስተማር የተማሪዎቹን ትኩረትና ፍላጎት በመሳብ የፅሁፍ ክሂል ችሎታን ማዳበር የተሻለ ውጤት ያመጣል ተብሎ በአጥዋ ታስቧል፡፡

## 2.1.2 የጽህፈት ችሎታ ምነንነት

የፅህፈት ችሎታ በእይታዊ (visual) ትምህርቶች (symbol) ውክልና በመገልገል ሰዎች ሀሳብ የሚለዋወጡበትና ተራክቦ የሚመሰርቱበት ተግባቦታዊ መሳሪያ ነው (Widdowson 1978 Hamer 1991)፡፡ ፅህፈት በተግባቦታዊ መሳሪያነት የተደረሰበትን ወይም የተጨበጠን እውቀት ማስተላለፊያ ብቻም ሳይሆን አዲስ ሀሳብ ማፍለቂያና መልዕክት መቀበያ እና በትምህርቶች ቀርፆ ማቆያ መንገድና ብልሀት ነው (Onadon and Buthem 1997):: Pincas (1982) ፅህፈትን ሲገልፁ በትምህርት አማካኝነት የሚቀሰምና ደረጃውን ጠብቆ ከሚደረግ ተከታታይ ልምምድ የሚገኝ ችሎታ ነው፡፡ ከዚህም ችሎታ ጋር ፅህፈት አዕምሮን እና እጅን ለማስተባበር ሃሳብን በተገቢው ምልክቶችና ቃላት በመወከል አንባቢ የግልም ሆነ የጋራ ገጠመኝን የማካፈል ችሎታ ነው ብለዋል፡፡

እንዲሁም Jordan (1991: 41) ይህንኑ ሀሳብ ሲያጠናክሩ ፅህፈት የሰው ልጆች እውቀቱን፣ ምኞቱን፣ ሃሳቡን ወዘተ ለመሰሎቹ ለመግለፅ የሚጠቀምበት የሚታይና ተቀባይነት ያለው መልዕክት ነው ይላሉ፡፡

ፅህፈት ሀሳብን በትምህርት ወይም በቋንቋ መወከል ሂደት ነው፡፡ ሂደቱን አካልንና አዕምሮን በማቀናጀት በአንድ ጊዜ በርካታ ባህሪያቱን ለምሳሌ ይዘቱን የአፃፃፍ ስልቱን የፅሁፍ መዋቅሩን፣ የቃላት ምርጫን፣ የሀሳብ አንድነትንግጥምጥምነትን ተከታታይነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወነውንና ከማሰብ ጋር ተቆራኝ ውስብስብ የአዕምሮ ስራ ነው (Nunan 1989:36) ከላይ ከቀረበው ምሁራን ሃሳብ እንደምንረዳው ፅህፈት ችሎታ በትምህርት ሚዳብርና በተከታታይ ልምድ በመታገዙ ሊጎለብት የሚችል ችሎታ መሆኑንና በዚህም ሰው ልጅ አዕምሮውንና አካሉን በማስተባበር እውቀቱን ገጠመኙን ሀሳቡን እና ውስጣዊ ስሜቱን በተገቢ ፅሁፋዊ መልዕክቶች በመወከል ለመሰሎቹ ሚያስተላልፉበት መንገድ መሆኑን ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ሆሂያትን በወረቀት ላይ በማስፈር ከፍ ያለው በአዕምሮ ውስጥ የሚፈልቀውን ሃሳብ በፅህፈት መልክ አቀነባብሮ ለአንባቢው መግለፅ ሂደት መሆኑ Bryne (1981:1) ጨምረው ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ ፅህፈት ለማንበብ ብቻ ተብሎ በወረቀት ላይ የሚሰፍር ሳይሆን ሀሳብና አመለካከት ለማድረስ የሚያስችሉ መልዕክትን በአንባቢው አዕምሮ ውስጥ የሚከሰቱ ስርዓት ባለው መንገድ የሀሳብ ችሎታቸውን ጠብቀው የሚቀነባበሩ ዓረፍተ ነሮችን አቀናጅቶ ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ፅህፈት በተዋረድ በተዋቀሩና አንድነትን በፈጠሩ ዓረፍተ ነገሮች አማካኝነት መግባባት ደረጃ ላይ ሊያደርስ የሚችል እንጂ መልዕክቶች፣ የቃላት ዓረፍተ ነገሮች ስብስብ ብቻ እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

Widdowson (1978 ፡ 62) በበኩላቸው የፅህፈትን ችሎታ ከንግግር ጋር በማነፃፀር በሚታዩ ስምምነታዊ ትምህርቶች (symbol) የሚገለፅ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ፅሁፋዊ ስርዓት መሆኑን ሲገለፅ (Raimes 1983 ፣ 5) በቃላት ውክልናና ወረቀት ላይ የሰፈረ እና ሕያው የሆነ ቋንቋ ነው ይላሉ፡፡ በሁለቱ ምሁራን ብያኔ መሠረት የፅህፈት ችሎታ መለያ ባህሪያቱ እይታዊ መልዕክትነቱ ለታላሚው ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ስርዓት ተገቢነቱን በቦታና በጊዜ ሳይወሰን ሕያው ሆኖ ሊቆይ መቻሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ፅህፈት በስሜት የሚከናወንና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሚጠናቀቅ ስራ አለመሆኑ በአንፃሩ ጌዜ ሚፈጅ፣ ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ፣ ሀሳብን መቀበል፣ መጠየቅና መመርመር በትኩረት ማሰብን የሚሻው የአዕምሮና የአካል ስራ መሆኑን ከተሰጡት ብያኔዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ መደበኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን የፅህፈት ችሎታን ለማዳበር በየፅህፈት ክሂል ማስተማር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## 2.1.3 የጽህፈት ችሎታ ትምህርት አስፈላጊነት

ከተለያዩ የፅሁፍ ቅርፆች ጋር መተዋወቅና ልምምድ በማድረግ የተለያዩ መማሪያ ስልትና ፍላጎትን ለመለየት አንዳንድ ተማሪዎች እንዲፅፉ የሚያደርግበት ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ተማሪዎች በቋንቋ አጠቃቀማቸው ለውጥ ለማግኘታቸው ተጨባጭ መረጃ ይሠጣል፡፡ መፃፍ እንደ አንድ የማስተማሪያ ችሎታ (ዘዴ ) ጥቅም ላይ ይውላል፣ ይህም የትምህርት አቀራረብ አሰልቺ እንዳይሆን ያግዛል፡፡ የተማሪውን በቋንቋ የመጠቀም ብቃት ያሳድጋል፡፡ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ክንዋኔዎችን በግልና በህብረት እንዲሰሩ ከማስቻሉም በላይ ለተማሪዎች እና ለመምህሩ ፀጥታናማሰቢያ ጊዜ በመስጠት ለተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚመች ጊዜ ለመፍጠር ያስችላል፡ ፡ እንዲሁም መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ፈተናዎችን ለማቅረብ ያገለግላል፤ ይህም በጣም በርካታ ተማሪ ቁጥር ሲኖር የቃል ፈተናን ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪ በሚሆንበት ወቅት ችግሩን ለመፍታት ተመራጭ መንገድ ነው፡፡

መፃፍ አስተሳሰብንና አድማስን የሚያሰፋ በመሆኑ ተማሪዎች እውቀታቸውን በመጠቀም ሀሳብ አመንጭተው በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ ካሉ አካላት ጋር መግባባትን የሚማሩበት ስለሆነ መፃፍ ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.1.4 ጽህፈትን የመፃፍ ብልሃት

የመፃፍ ተግባር የሚከናወን በትአጠቃላይ ሁኔታ የተግባር አካባቢ የፀሀፊውን የረጅም ጊዜ የመረጃ ክምችትና የመፃፍ ሂደትበማለት (Lindoife (1985,155) እና Brown (1985,12) በስዕልያሰፍሩታል፡፡ተግባር አካባቢ የሚሉት ሞዴላቸው መሠረት ተማሪዎች እንዲፅፉ የሚሰጣቸው ትዕዛዝ ርዕሰ ጉዳይ አንባቢ ለመፃፍ የሚያነሳሳቸ ውሁኔታ ናየፀሐፊው ፅሁፎች ናቸው፡፡

የፀሐፊው ረጅም ጊዜ መረጃ ክምችቶች ደግሞ ፀሀፊ ውስለ ሚፅህፍበት ርዕስ ስለአካባቢው ናስለ መፅሀፉ ሂደት ያለው እውቀት ነው የመፅሀፍ ሂደት ግንማቀድማ ደራጀት ዓላማ መወሰን መከለስን ማንበብንና ማረምን ሁሉ ያካትታ ልፅሀፊት ንመጥሀፍ ሂደት ውስጥ ተመልሶ ማየት ወይም ወደኃ ላመመለ ስሁኔታ ሊኖርይች ላልፀሐፊው ከአንድ ሃሳብ ተነስቶ ለመግለፅ የተፈለገውን ነገር በፅሁፍ ለማስተማር ለማስተላለፍ ሲሉ መፃፍ ይጀምራሉ፡፡ነገር ግን በመፃፍ ሂደት ውስጥ እጠየቁቆም ይላሉ ቆም ሚሉበት ደግሞ ሆነብለው ወይም ተገደው ሊሆን ይችላል የመፃፍ ብልሀት እንደየፀሀፊውየሚለያይ ቢሆንበፀሀፊውሂደትግንበሁሉምአዕመሮውስጥሚከናወንሀሳብየማመንጨትመረጃንመምረጥናማ ቀናጀት የማቅረብ፣የመከልከል ናማረም ሂደት በመሆኑም ሁንም ያስማማል በዚህ ሂደት ውስጥም ለማለፍ፣ መጠየቅመመርመር፣ ፍቺመስጠት፣ቃል ወይንም ሀገርን መምረጥ መካተት ወዘተ ይኖራሉ (Wenden (1991)፡፡ ግጥም የፅሀፊትን መፃፍ ሂደት ውስጥ ወደ አዕመሮ ከሚመጡት ኃሳቦች በጥቂቱ መምረጥመላመምታትማወዳደርናማብራራት፣አዲሱን መረጃ ቀድሞ ከአምሮ ከነባር መረጃ ጋር ማዋሐድ ወዘተና በመጨረሻም የተለያየ መረጃዎችን በአንድነት በማቀናጀት መፃሐፍ የመፃፍ ብልሀት በመሆኑ ይገልፃሉ፡፡ አያይዘውም ለፀሐፊው ወይም ለተማሪው መስጠት ስለሚገባው የመፅሃፍ ነፃነት ስለተግባቦት ማሰብ በመፃፍ ብልሀት የሚካተቱ መሆናቸዉን ያስረዳሉ፡፡ (Golubel 1986) በበኩላቸው ሃሳብን ጨምቀው ማውጣት በቅድም ተከተል ማስቀመጥ በዓይነት መመደብ ማደራጀት መተንበይ መጠቀም ማረጋገጥ የተለያዩ ሀሳቦችን በአንድነት ማቀናጀት መገምገም ሁሉን የሚያሳብ ክሂል በሚሉት መፅሀፍ ብልሀት ስር እንደሚካተቱ ይገልፃሉ የመፅሀፍ ብልሀትን ተማሪው ሃሳቡን በመግለፅ በአላማው መገኘት በንቁም ሆነ በኢ-ንቁ (conscious and uncoscicous) መንገድ የሚጠቀምበት ሂደት ነው፡፡ በታላሚው ክሂል donsim ወይም ለመስራት ክፍት የሚደረግበት ዘዴ መሆኑን Richards and Rodgers (1986) እና Richats John and Weber (1985 ) ይደርሳሉ::

Laibe( 1991 የመፃፍ ስልትን በተለያ ክፍሎች መጀመሪያም ሚፃፍበት ሃሳብ ሚያፈልቅ ደረጃ ሲሆን በዚህ ርዕስ መተወር ሲሆን (the orizing) ገጠመኝ ምልከታና በምክንያት ማደራጀት ይጠቀሳሉ ሁለተኛው የተገኘው መረጃ ማደራጀት ነው፡፡ በዚህም መዋቅር (structure) ቅርፅ (form) ቅደም ተከተል (sequene) ይገኛሉ፡፡ ሶስተኛው

በቃላትና በዓረፍተ ነገር ተጠቅሞ ሀሳብን ማስተላለፍ ወይም መግለፅ ነው፡፡ መጨረሻው ክንውን ሲሆን ይህም ተጠናቆ ሚቀርበብት ፅሁፍ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻል የፅሁፍ ብልሀት በፀሀፊው ወይም በተማሪው አዕምሮ ውስጥ ከሚመላለሰው ሀሳብ መረጃን መምረጥና ማቀናጀት ያንንም ማደራጀት መጀመሪያውን ረቂቅ መፃፍ መሰብሰብ፣ ማረም ከዚያም የመጨረሻውን ፅሁፍ እስከ ማጠናቀቅ ድረስ ያለውን ሂደት መሆኑ ነው፡፡

## 2.1.5. የመጻፍ ክሂል በአፍ መፍቻ እና በሁተኛ ቋንቋ ትምህርት

የመጻፍ ክሂል በአፍ መፍቻ እና በሁተኛ ቋንቋ የትምህርት ውስጥ ጉልህ ልዩነት ይህውም ፡፡ በሁለቱም የትምህርት አውዶች(በአፍ መፍቻ እና በሁለቱም ቋንቋ) ተማሪው የመጻፍ ክሂል መለማመድ የሚጀምረው በትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ ሲማር ነው፡፡ ነገር ግን በመማር ሂደት ውስጥ ከሚፈጠሩ አውዶች አኳያ በሁለቱም መካከል ልዩነት የሚታይባቸው ይመስላል፡፡ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ሂደት ያላቸውን የቀደመ እውቀት ወይም ማኅበረሰባቸውን መሰረት አድርገው እንዲጽፉ ሰፊ እድል ይፈጥርላቸዋል (Byrne 1988 እና Silva 1990)፡፡ ስለሆነም ታላሚው ቋንቋ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የማኅበረሰቡን የቋንቋ አጠቃቀም ምን እንሚመስል በአቅራቢያቸው የሚያገኙበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህም በመጻፍ ትምህርት ሂደታቸው ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ ይፈጥርላቸዋል ተብል ይታሰባል ፡፡ በሌላ በኩል በሁለቱም ቋንቋ ትምህርት ጊዜ ምናልባት የታሊሚው ቋንቋ ማኅበረሰብ በቅርብ የማይኖርበት ሁኔታ ስለሚያጋጥም በዚሁ የተነሳ የቋንቋ አጠቃቀሙን በሚፈለገው መልኩ መለየት አዳጋች ይሆናል ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በመጻፍ ትምህርት

ሕይወታቸው ችግር ሊገጥማቸው ይችላል (Silva 1990) ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመጻፍ ክሂልን እንደውጭ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ማህበረሰብ ባህል፣ እሴት፣ ልማድ፣ ወዘተ... በአቅራቢያቸው የማግኘታቸው ሁኔታ ዝቅተኛ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የቋንቋውን ማህበረሰብ መሰረት በማድረግ የመጻፍ ተግባርን እንዲያከናውኑ ተጽዕኖ ያደርግባቸዋል፡፡ በዚህም ጊዜ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚያውቋቸውን የግል ልምዶች ወይም ገጠመኞች ወይም በሁለቱም ቋንቋቸው(የውጭ

ቋንቋ) በመተርጎም የመጻፍ ክሂልን መለማመድ እንደሚችሉ Silva (1990) ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም ግን ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚያውቋቸውን የቀደሙ ልምዶች በሁለተኛ ቋንቋ መተርጎም በሚጥሩበት ጊዜ ከቃላት አጠቃቀም እና ከሀሳብ አደረጃጀት አኳያ ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችሉ Grabe and Kaplan

(1996) ያስረዳል፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ በአፍ መፍቻ እና በሁተኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት መካከል ልዩነት እንደሚስተዋል መረዳት ይቻላል፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የመጻፍ ክህል መማር፣ ተማሪዎች ገጠመኞቻቸውን እና የታላሚውን ቋንቋ ማህበረሰብ አውድ የማወቅ ሁኔታ ስለሚኖራቸው ሀሳባቸውን አደራጅተው መጻፍ አመቺ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል፡ በአንጻሩ የመጻፍ ክሂልን እንደሁለተኛ/የውጭ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋውን ማህበረሰብ በቅርብ የማግኘታቸው ሁኔታ ዝቅተኛ የሚሆንበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪዎች የማህበረሰቡን የአኗኗር ሁኔታ መሰረት አድርገው በሚፈለገው መልኩ ሀሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡ በመጻፍ ክሂል ላይ በመመስረት ከአፍ

መፍቻ እና ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር ተያይዞ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ በዚህ የጥናት ሂደትም አማርኛ ቋንቋ በስፋት በአፍ መፍቻ ቋንቋነት በሚነገርበት ቦታ ላይ ትኩረት በማድረግ በመጻፍ ትምህርት ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ውጤታማነቱን እንዲፈትሽ ተርጓል፡፡

## 2.1.6. የጽህፈት ክሂል ችሎታን ማቀድና የማስተማር መርሆች

ተማሪዎች በፅሁፍ አማካኝነት ሃሳባቸውን በተገቢው ሁኔታ የመግለፅ ሁኔታን እንደሚያሳድጉ ለማድረግ መምህራን የፅህፈት ክሂል ችሎታን በሚያዳብሩና ሰዋሰዋዊ ቃላት ችሎታን በሚያጠናክሩ መልመጃዎች ላይ በማተኮር ትምህርቱን ማቅረብ እንዳለባቸው በተግባራዊ ሂደቱ መርሆች የሚከተሉትን መርሆዎች ማስታወስ ተገቢ እንደሚሆን (Atkins 1996:11) ይገልፃሉ፡፡ የፅሁፍ ክሂል በክፍል ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ የሚለማመዱት መሆን አለበት፡፡ በክፍል ውስጥ የሚመደበው ክፍለ ጊዜ ለሰዋሰውና ለቃላት ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች መልመጃዎችን መሰረት በማድረግ የመፃፍ ክሂላቸው ማዳበር አለባቸው፡፡ በዚህ ውስጥ የሚተገበሩት አስደሳችና ለመፃፍ የሚያነሳሳ ኣላማ ያላቸው ተማሪዎ የቋንቋ ደረጃ እና ልምዳቸውን

ያገናዘበ ሀሳቦችን በቀላሉ እንዲገልፁ የሚያስችል ለውይይት በቡድን ለመፃፍ ተስማሚ የሆነ ግልፅ መመሪያዎች ያሉትና የሚያበረታታ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ ተማሪዎች እንዲፅፉ ከመፈለጋችሁ በፊት ማነሳሳት በግል በጥንድ ወይም በቡድን እንዲሰሩ ከተፈለገ በቅድሚያ በግልፅ ሊነገራቸው ይገባል፡፡ መልመጃዎች ሲከናወኑ መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ በቁጥጥር ወቅት ጠቃሚና ገንቢ ምላሽ (feedback) መስጠት፡፡ ለምሳሌ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ያሉትን መለየት ድጋፍ መስጠት ማድነቅና ማበረታታት፣ ፅሁፋቸውን ማረም አስተያየት መስጠት፣ ተማሪዎች መፅሀፍ ከሚፈለግነባቸውን ሃሳቦች በመቀበል በተቻለ መጠን ግልፅና ትክክል በሆነ መንገድ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማበረታታት ሀሳባቸውን በፅሁፍ መግለፅ ችሎታቸው ከተፈለገው ደረጃ ላይ ከደረሰ ሊፈተኑ የሚችሉ አዝናኝና ልቅ ያልሆኑ ውስን መልመጃዎችን ማቅረብና ተማሪዎች እርስ በእርሳቸው እንዲፅፉ ማበረታታት የጻፉትን ፅሁፍ ተቀያይረው እንዲያነቡና አስተያየት መስጠት ማድረግ የሚሉ ይገኙበታል፡፡

## 2.1.7. ግጥምን በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ

እንደ ስነፅሁፍ ዘርነቱ ግጥም ለተማሪዎች የሚያበረክታቸው በርካታ ጥቅሞች እንዳሉ የሚያረጋግጡ ጥናቶች ይገኛሉ፡፡ ምትና ዜማዊነት፣ የቃላት ድግግሞሽ፣ አጭር አቀራረብ፣ ምስል ከሳችነቱ፣ የንባብ ተነሳሽነት ለመፍጠር መስህባዊነቱ የፅሁፍ ችሎታን ለማዳበር ለማስተማር ተመራጭ ያደርገዋል፡፡ በቋንቋ ክፍል ውስጥ በግጥም የፅሁፍ ችሎታን ማዳበርለማስተማር ፋይዳ በ Gill(2007)፣ Alexander (2017) Lewis (2015)፣ Porath (2014) እንደተጠቀመው ረጅም እድሜ ያስቆጠረ ከስነፅሁፍ አስቀድሞ የኖረ (ስነቃላዊ ዘውጉ) የሰው ልጆችንባህሪናድርጊት፣ የተፈጥሮን ክስተት ባማሩ አጫጭር አቀራረቦች ያቀርባል፡፡ የግጥም ፀሀፊዎች በአምሮአቸው የሚያስቧቸውን ጉዳዮችና የህይወት ምልከታዎቻቸዉን አውድ ከስተው፤ ቃላት መጥነው፤ ማራኪነት አላብሰው፤ ስለሚያቀርቡ መስህብነታቸው ጉልህ ነው፡፡ ይህ የግጥም ባህሪ ፀሀፊውንና አንባቢውን በግጥም የፅህፈት ችሎታን ለማዳበር መድረክ በማግኘት እየተሰላቹ ሳይሆን እየወደዱ መጻፍን እንዲሁም የፅህፈት ችሎታ ክሂልን እንዲያዳብሩ ማበረታታትን ይፈጥራል፡፡ ይህ አስተዋፅኦ የፅህፈት ችሎታን ማዳበር ብልሀቶች በሚገባ ከታገዘ ተማሪዎች በግጥም የፅህፈት ችሎታን ማዳበር ተወዳጅ ልምዳቸው እንዲያደርጉት ዘላቂ መነሳሳት ይፈጥርባቸዋል፡፡

ዘሪሁን (1992) ከፍ ሲል ከቀረበው ገለፃ ጋር በተዛመደ መልኩ ሲገልፁ፣ ይህ የስነፅሁፍ ዘር አዕመሮአዊ፣ስሜታዊ እና ምናባዊ ከመሆኑም በላይ እንደሌሎች የሥነጽኁፍ ዘርፎች ዋነኛ ትኩረቱ በሰው ልጅ ሂወት ላይ ነው፡፡ ግጥም የሰውን እለት ተዕለት ገጠመኝ ስሜት በሚነካ፣ በሚመስጥና በሚያስደስት ስልት ያቀርባል፡፡ ገጣሚው በህይወት ውስጥ ካሉት ምስቅልቅና ባለብዙ ዘርፍ ሁኔታዎች በስዕል ምልከታው የታዘበውን፣ ልቡ ያሰበውናን ልቡ ያረፈበት ስሜቱን የቆጠቆጠውን መርጦ በራሱ ፈጠራ አዋቅሮና አቀናጅቶ ሁነኛ ትርጓሜ በመስጠት ለሰሚው ወይም ለአንባቢው ያቀርባል፡፡ይህ ሁነኛ ትርጓሜ ከገጣሚው ሁነኛ አስተያየት የመነጨ የስሜቱ ነፀብራቅ ቢሆኑም ለሰሚው አዲስ እውቀትና ገጠመኝ ያስገኝለታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህም አለሙን በይበልጥእንዲገነዘብና እንዲያጤን ያደርገዋል ብለዋል፡፡በተጨማሪም ከግጥም የሚገኘው እውቀት ከራሱ ገጠመኝና ከማህበረሰቡ ልዩ ልዩ እሴቶች ጋር በማደባለቅ ያጤነ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ግጥም በባህሪው ገላጭና አዛኝ በመሆኑ በተራው ለማየት ያልቻልነውን ውበቶች የህይወት ሚስጢሮች እንድንመለከት እድል ይሰጣሉ ሲሉ የግጥምን የስሜት ቅርበትና የተገቢነት መጠነ ርዕይጠቁመዋል፡፡

Williams (2004) በበኩላቸው እንደገለፁት የህይወት ተሞክሮ ለማበልፀግና የቋንቋ ክሂሎችን አጠናክሮ ለማስተማር ምቹ ነው፡፡ ግጥምገላጭ በሆኑ ቃላትና በአጫጭር መስመሮች ስለሚገነባ የፅህፈት ችሎታን ከማዳበር ጋር ዘላቂ በሆነ ሁኔታ ተዛምዶ ቢቀርብ የተማሪዎችን የፅህፈት ችሎታን በማዳበር ረገድ በከፍተኛ ደረጃ ይረዳሉ፡፡ ተማሪዎች የሚከብዷቸውን ፊደላት በመረጻፍ እንዲለማመዱ ያደርጋል፡፡

(2012) እንደገለፁት የፅሀፊት ችሎታን ማዳበር አያይዞ ማስተማር ሲታሰብ ዋናው አ ሳ ሳቢ ጉዳይ የሚቀርበው ግጥም ለተማሪዎቹ የቋንቋ ችሎታ ልምድ እን ግንዛቤ ያለውን ተመጣጣኝነት ታሳቢ በማድረግ ነው ለዚህም እንደትምህርት ቤት አይር ሁነኔታ፣ እንስሳት ወቅቶች ቤተሰብ ጓደኛ ወ ዘተ ያለ ቀለል ያሉ ብ ይዘቶች ያላቸው ርዕሶችን የፅ ህፈት ች ሎተሰነረ ማደበር በመማሪያ አው ድ በማስተማር መጀመር ያስፈልጋል ከዚህም ጋር ተማሪዎች በግጥም የፅህፈት ችሎታን ማዳበር እነህዲችሎ ልዩ ልዩ የፅህፈት ችሎታን ማዳበር ብልአቶ ችን ከማሰልጠን ጋር ከግጥም በመፃፍ እንዲበረታቱ ማድረግ አስ ፈላጊ ነው በ ግጥም የፅ ህ ፈት ችሎታን ማዳበር ጋር በማቆራኘት ተማ

ሁለንተናዊ እውቀትና የቀ ደመ ምድ በተደራጀ ሁኔታ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች የቀረበ እውቀትና መረጃን መተንተን ላይ ነው

## 2.1.8. የጥናቱ ንድፈ-ሀሳባናዊ ማዕቀፍ

ስነ-ልቦናዊ የቋንቋ ትምህርት አተያይ የተመሰረተው ሁለንተናዊ ዕዉቀትና የቀደመ ልምድ በተደራጀ አኳኃን በተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች የቀረበ ዕዉቀትና መረጃን በመተንተን ላይ ነዉ፡፡ የአዕምሮ ንድፎች የፅህፈት ችሎታን ለማዳበር ፅንሰ ሀሳቦችን፣ የቃላትና የሀረጋት አፃፃፎችን እንዲለዩ እና ግጥምን በመፃፍ በሚፈጥረው ልዩ ስሜት፣ በምቱ፣ በድምፀቱ፣በሀሳብ ፍሰቱ ወዘተ ተደሳች እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ የአዕምሮ ንድፎች የፅህፈት ችሎታን ለማዳበር በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በመጻፍ ሂደት አዕምሮ መረጃዎችን ለመተንተን የሚከተለውን ስልት ይወስናሉ፡፡ ተማሪዎች አንድን የፅህፈት ችሎታን ለማዳበር የቀረበን ፅሁፍ በተለየ መንገድ ሊረዱት ይችላሉ፡፡ ይህም የሚሆንበት አንደኛ ምክንያት የተለያዩየአዕምሮ ንድፍ፣ እውቀትና ንቃት ደረጃ ግለሰባዊ ልዩነቶች የሚታይበት በመሆኑ ነው፡፡ Churchill (2013) የዐዕምሮ ንድፍ (schemata) በግለሰባዊ ደረጃ የተያዘ, የቀደመ ዳራ እውቀትና መረጃ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ይህ ዳራዊ እውቀት አንድን የቀረበን ፅሁፍ በሚገባ ለመፃፍ ወሳኝ ነው (Claros, 2008):: በዚህ መሰረት የአዕምሮ ንድፈ ሀሳብ በተለዩዩ ጠቃሚ ችሎታን የማዳበር ስርአቶች በመታገዝ አንድን የቀረበን ፅሁፍ በጥሩ ሁኔታ ለመፃፍ ብሎም በሀሳቦች መካከል ያሉ ግንኙቶችን ለመለየት ጠቀሜታ አለው፡፡

ሆኖም ግን ስነልቦናው የቋንቋ ትምህርት አተያይ ትኩረት የሚሰጠው በዋነኝነት ለውስጣዊ ሁኔታ እንጅ በዊጫው ሁኔታ አደለም በማለት 2008 1979 በመጥቀስ በስነልቦናዊ ቋ ትምህርት አተያይ ላይ ትችት ይንፀባረቃል ይህም ሁኔታ ለማህበራዊ -ባህላዊ ንድረፈ ሀሳብ ተጠናከሮ በመምጣት ምክንያት ሆኖዋል እንድ ---2013 ማህበራዊ ባህላዊ ንድ ፈ ሀሳብ ትጀለኩረት በማግር ሂደት በማህበራዊ አውድ ተፅ ኖ እንደሚደረግበትና ማህ በራዊ ተ ለዋውጦዎች የመማር ሂደት ላይ የራሳ ቸው ጫና የሚያሳድሩ በመሆን ነው እንደ --- እንደገለፁት ተራክቦ (የቋንቋ አጠቃቀም ) የቋንቋ ትምህርት አንዱ ዋነኛው አስፈላጊ ጉደፋይ ነው ስለሆነም ማህ በራዊ ክበነንውኖች እንደውጫዊ ተ ግባራቸው ለአዕምሯዊ ሂደቶች ምንጭ ናቸው ተማሪዎች እርስ

በእርሳቸው ተራክበዊ አዕምሯቸው ይነቃቃል በመሆኑም በቋንቋ ጽምጎርጽ ሂደት ተማሪዎች ተግባራቱ ን ሊያከናውኑ የሚችሎት ከቀደመ እውቀታቸው እና ከመሰረቱት ልምድ ከመነሳት በነው ማህበራዊ - ባህላዊ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ነባር ግለሰባዊ ሂደት ሳይሆን በማህበራዊ አውድ በአቻዊ ተሳትፎ እና የቋንቋ መምህሩ ሞያዊ ችሎታ ላይ የሚገባ ክንዋኔ የማህበረ ባህላዊ ንድፈ ሀሳብ አንቸዱና ዋንኛው ትኩረቱ የመማር ክንዋነቤን በተሳትፎ ወይም በተራክቦ አማካኝነት ማመቻችት በነው ----2013 ከዚህ አንፃር የፅህፈት ችሎታን ማዳበር እንደማህበራ ዊ ክሂልነቱ ተማራዎች ተራክቦዊ ሂደቶች ከአቻቸው ጋርና ለከመምህራቸው ጋር ንቁ ተሳትፎ በማካሄድ ይማራሉ

ከዚህ በመነሳት ሙከራዊ ጥናት ከስነልቦናዊ የቋንቋ ትምህርት አተያ ይልቅ በማህበራዊ ንድፈ ሀሳብ ትኩረት ያደርጋሉ ምክንያቱ ስነልቦናው ቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳብ በግለሰባዊ የአዕምሮ ችሎታ ላይ ተ መሰረተ እና የግል ኩክክርን የሚደ ግፍ ሲሆን ማህበረ ንድፈ ሀሳብ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ማህበራዊ ተሞክረዋቸውን ግንዛቤያቸው ላይ በመመርኮዝ የቀደመ እውቀታቸውንና ልምሰደዳቸውን በመጠቀም እርስ በእርስ ከሚፈጥሩት ተራክቦ በመነሳት እርስ በእርስ በመማር በራሳቸው እውቀታቸውን እያሻሻሉ ይሄዳሉ የሚል እምነት በመያዙ ነው በግጥም የፅህፈት ችሎታን ማዳበር ከተማሪዎች ማህበራዊ ሄኔታ የፈለቀ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ስለሚመሰተር ተማሪዎች በግል በያዟአች ዳራዊ እውቀቶች ተሞክሮዎችና መረጃዎች ዙሪያ ተሞክሮ በማካሄድ በተሸለ ሁኔታ የፅህፈት ችሎታን እንዲያዳብሩ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥርላቸዋል ተ ብሎ ይታመናል መርጦ ተሳታፊ ማድረግ ነው፡፡

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ስነ ጽሑፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ያለውን ውጤታማነት በሙከራ የመረመሩ የአማርኛ ቋንቋ ጥናቶችን አጥኚዋ ለመቃኘት ሞክራለች፡፡ በጥናት ቅኝቷም በአንድም ሆነ በሌላ ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸው ሶስት የአማርኛ ቋንቋ ጥናቶችን ማግኘት ችላለች፡፡ ጥናቶቹም ገሊላ (2010)፣ ታዛነህ (2012) እና ፍሬሕይወት (2013) ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ጥናቶቹ ከዚህ ጋር ተዛምዶ ቢኖራቸውም በጥናቶቹ ክፍተቶችን አግኝታለች፡፡ በመቀጠል ሶስቱ ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡

የመጀመሪያው ተዛማጅ ጥናት ገሊላ (2010) ሲሆን ‹‹ስነ ጽሑፋዊ እና ስነ ጽሑፋዊ ያልሆኑ ምንባቦች አንብቦ የመረዳት ክሒልን ከማዳበር አንጻር ያላቸው ሚና (ሙከራዊ ጥናት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)›› የሚል ርዕስ አለው፡፡ የገሊላ ጥናት የተሰራው በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ሲሆን ዓላማውም ‹‹ስነ ጽሑፋዊ እና ስነ ጽሑፋዊ ያልሆኑ ምንባቦች አንብቦ የመረዳት ክሂልን ከማዳበር አንፃር ያላቸውን ሚና ማነፃፀር›› የሚል ነው፡፡

ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2010 ዓ.ም በ9ኛ ክፍል በመማር ላይ በነበሩ ተማሪዎች ላይ ሙከራዊ ጥናት ተከናውኗል፡፡ በጥናቱም ከተመረጡት ሁለት የ9ኛ ክፍል ምድቦች ውስጥ አንዱ ስነ ጽሑፍን በመጠቀም፣ ሌላኛውን ምድብ ደግሞ ስነ ጽሑፋዊ ያልሆኑ ጽሑፎችን በመጠቀም የማንበብ ክሒልን ተምረዋል፡፡ ከጥናቱ በኋላ ከተፈተኑት ፈተና የተገኘው ውጤት ተወስዶ የመረጃ ትንተና የተከናወነ ሲሆን የመረጃ ትንተናው እንደሚያሳየው ስነ ጽሑፋዊ ጽሑፎችን በመጠቀም የተማሩት ተማሪዎች ስነ ጽሑፋዊ ባልሆኑ ጽሑፎች የተማሩት ተማሪዎች የበለጠ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው፡፡ በዚህም ስነ ጽሑፍ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ አስተዋጽዖ እንዳለው ተረጋግጧል፡፡

ይህ ጥናት እና የገሊላ (2010) ጥናት ከገሊላ ጥናት ጋር ያለው ዋና መመሳሰል ሁለቱም ስነ ጽሑፍን በቋንቋ ማስተማሪያነት ያለውን ጠቀሜታ በሙከራዊ ጥናት የመረመሩ ጥናቶች መሆናቸው ነው፡፡ ይህንን ተከትሎም የሁለቱም ጥናቶች ንድፍና አይነት ተመሳሳይ ሊሆን ችሏል፡፡ በተጨማሪም የሁለቱም ጥናቶች መረጃዎች የተሰበሰቡት በፈተና ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ይህ ጥናት ካለው የትኩረት አቅጣጫ አንጻር በገሊላ ጥናት የተስተዋሉ ሁለት ክፍተቶችን መሙላት ችሏል፡፡ አንዱ ክፍተት ከገሊላ ጥናት በተለየ ከስነ ጽሑፍ ዘውጎች ውስጥ ግጥምን ብቻ በመምረጥ በሙከራ የፈተሸ ጥናት መሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም የገሊላ ጥናት ትኩረቱን ያደረገው በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የገሊላ ጥናት ያላካተተውን የመጻፍ ክሂል ማካተቱ ሁለተኛው ክፍተት ነው፡፡ ስለሆነም ሁለቱ የገሊላ ጥናት ክፍተቶች በዚህ ጥናት ተዳስሰው የጥናቱ ክፍተት ተሞልቷል፡፡

ሁለተኛው ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመደው የአማርኛ ቋንቋ ጥናት በታዛነህ (2012) የተሰራው ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስ ‹‹ስነ ፅሁፋዊና ኢ-ስነ ፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአማርኛ

ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማሻሻል ረገድ ያለቸው ሚና (በአዴት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በዘጠኛ ክፍልተተኳሪነት)›› የሚል ነው፡፡ የታዛነህ ጥናት የተሰራው በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ነው፡፡ የጥናቱ ዓቢይ ዓላማም ስነ ጽሑፋዊ እና ኢ. ስነ ጽሑፋዊ የሆኑ ምንባቦች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበት ከሁለቱ የምንባብ አይነቶች የበለጠውን መለየት የጥናቱ ንዑስ ዓላማ ነው፡፡

እነዚህን ሁለት ዓላማዎች ለማሳካትም ከፊል ሙከራዊ ጥናት ተከናውኗል፡፡ ተጠኚዎቹም በአማራ ክልል፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን፣ በአዴት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2012 ዓ.ም በመማር ላይ የነበሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በተጠቀሰው ትምህርት ቤትና የትምህርት ዓመት በመማር ላይ ከነበሩ 915 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ 102ቱን በእድል ሰጭ ንሞና ዘዴ ከተመረጡ በኋላ የተመረጡት ተማሪዎች በሁለት ምድቦች ተመድበው ከፊል ሙከራዊ ጥናት ተከናውኗል፡፡ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንዳመለከተው ስነ ጽሑፋዊ ምንባቦች ስነ ጽሑፋዊ ካልሆኑት ተማሪዎች የበለጠ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማሳደግ ችሏል፡፡

የታዛነህ (2012) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተመሳስሎ ሁለቱም ስነ ጽሑፍን በቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ያለውን ጠቀሜታ በሙከራዊ ጥናት የመረመሩ ጥናቶች መሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም የሁለቱም ጥናቶች ንድፍና አይነት ተመሳሳይ ሲሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን ያገለገለው ፈተና እና መተንተኛ ዘዴዎቹም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ጥናት ካለው የትኩረት አቅጣጫ አንጻር በታዛነህ ጥናት የተስተዋሉ ሁለት ክፍተቶችን መሙላት ችሏል፡፡ አንዱ ክፍተት በታዛነህ ጥናት ተነጥሎ ያልተሞከረውን ግጥም የተሰኘው የስነ ጽሑፍ ዘውግ ነጥሎ በሙከራ የፈተሸ ጥናት መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም የታዛነህ ጥናት ትኩረቱን ያደረገው በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የታዛነህ ጥናት ያላካተተውን የመጻፍ ክሂል ማካተቱ ሁለተኛው ክፍተት ነው፡፡ ስለሆነም ሁለቱ የታዛነህ ጥናት ክፍተቶች በዚህ ጥናት ተዳስሰው የጥናቱ ክፍተቶች ተሞልተዋል፡፡

የመጨረሻው ተዛማጅ ጥናት በፍሬሕይወት (2012) የተሰራው ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስ ‹‹ስነ ጽሑፋዊ የሆኑ እና ስነ ጽሑፋዊ ያልሆኑ ምንባቦች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት

ችሎታ ለማዳበር ያላቸው አስተዋጽዖ (አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ በፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)›› የሚል ነው፡፡ ጥናቱ የተሰራው በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማም ስነ ጽሑፋዊ እና ኢ ስነ ጽሑፋዊ የሆኑ ምንባቦች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡

ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስም አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱና በወለጋ አካባቢ በ2013 ዓ.ም በመማር ላይ የነበሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ከፊል ሙከራዊ ጥናት ተከናውኗል፡፡ በጥናቱም ስነ ጽሑፋዊና ስነ ጽሑፋዊ ያልሆኑ ጽሑፎችን በመጠቀም የማንበብ ክሒልን በማስተማር ጽሑፎቹ በተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያመጡት መሻሻል ተገምግሟል፡፡ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንዳመለከተውም ስነ ጽሑፋዊ ጽሑፎች ስነ ጽሑፋዊ ካልሆኑት የበለጠ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያሳድጋል፡፡

የፍሬሕይወት (2013) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተመሳስሎ ሁለቱም ስነ ጽሑፍን በቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ያለውን ጠቀሜታ በሙከራዊ ጥናት የመረመሩ ጥናቶች መሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም የሁለቱም ጥናቶች ንድፍና አይነት ተመሳሳይ ሲሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን ያገለገለው ፈተና እና መተንተኛ ዘዴዎቹም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ጥናት ካለው የትኩረት አቅጣጫ አንጻር በፍሬሕይወት ጥናት የተስተዋሉ ሁለት ክፍተቶችን መሙላት ችሏል፡፡ አንዱ ክፍተት በፍሬሕይወት ጥናት ተነጥሎ ያልተሞከረውና ግጥም የተሰኘው የስነ ጽሑፍ ዘውግ በዚህ ጥናት ተነጥሎ ውጤታማነቱ በመፈተሹ ነው፡፡ በተጨማሪም የፍሬሕይወት ጥናት ትኩረቱን ያደረገው በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የፍሬሕይወት ጥናት ያላካተተውን የመጻፍ ክሂል ማካተቱ ሁለተኛው ክፍተት ነው፡፡ ስለሆነም ሁለቱ የፍሬሕይወት ጥናት ክፍተቶች በዚህ ጥናት ተዳስሰው የጥናቱ ክፍተቶች ተሞልተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተቃኙት ሶስት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱ ጥናቶች ናቸው፡፡ ሶስቱም ተዛማጅ ጥናቶች ዋና ትኩረት ያደረጉት ስነ ጽሑፍን በቋንቋ ማስተማሪያነት ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መገምገም ላይ ነው፡፡ የሶስቱም ጥናቶች ውጤት የሚያሳየው ስነ ጽሑፍን በቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጉልህ ያሳድጋል፡፡ ምንም እንኳን ሶስቱ

ጥናቶች በተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ ዘመናት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ የተሰሩ ጥናቶች ቢሆኑም ከጥናቶቹ የተገኘው ውጤት ግን ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህም ስነ ጽሑፍ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከማሳደግ አንጻር ሰፊ ዓውድ እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ሶስቱ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች ላይ በማተኮራቸው ቢመሳሰሉም በሶስቱም ጥናቶች ያልተካተቱ ሁለት ክፍተቶች በዚህ ጥናት ተሞልተዋል፡፡ ክፍተቶቹም ከስነ ጽሑፍ ዘርፎች ውስጥ ግጥም ለብቻው ተነጥሎ በሶስቱም ጥናቶች አለመሞከሩና በሶስቱም ጥናቶች የመጻፍ ክሂል አለመካተቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ክፍተቶች በዚህ ጥናት በመሞላታቸውም ሶስቱ ጥናቶች ከተለያዩ ጉዳዮች አንጻር ሰፊ ዓውድ እንዲኖራቸው ማድረግ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሒል ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካትም ከፊል ሙከራዊ ጥናት (quasi experimental research) ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከጥናት አይነት አንጻር ይህ ጥናት መጠናዊ ምርምርን (quantitative research) በመከተል የተከናወነ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ አይነት መጠናዊ የሆነበት ምክንያትም ለጥናቱ በግብዐትነት ያስፈለጉት መረጃዎችና መረጃዎቹ የተተነተኑባቸው መንገዶች መጠናዊ በመሆናቸው ነው፡፡

በዚህም መሰረት ለጥናቱ የተመረጡት ሁለት የ9ኛ ክፍል ምድቦች ላይ ጥናቱ ተከናውኗል፡ ፡ በመጀመሪያ የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ምንም ትምህርት ከመማራቸው በፊት ቅድመ ትምህርት ተፈትነዋል፡፡ በመቀጠልም የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን ግጥምን በመጠቀም፣ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎችን ደግሞ በ9ኛ ክፍል በሚገኙት ማስተማሪያዎች ለ10 ክፍለ ጊዜዎች ተምረዋል፡፡ በመጨረሻም የተማሪዎቹን የመጻፍ ክሒል የሚመዝን ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸው የተገኘው ውጤት ተተንትኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው ከተብራራ በኋላም ትንተናው የሚያመለክተውን ውጤት መሰረት በማድረግ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሒል ለማሳደግ ያለው ሚና ተመርምሯል፡፡

## 3.2. የናሙናዎች አመራረጥ

ይህ ጥናት ከፊል ሙከራዊ የአጠናን ስልትን ተከትሎ የተከናወነ ጥናት እንደመሆኑ የማጥኛ ስፍራ፣ ተጠኚ ተማሪዎች እና የሙከራ ትምህርት የሚያስተምር መምህር መመረጥ ነበረባቸው፡፡ ይህ ተግባር መከናወን ያለበትም የጥናቱን ዓላማ መሰረት ያደረጉ የንሞና ዘዴዎችን (sampling method) በመጠቀም ነው፡፡ በመቀጠልም የማጥኛ ስፍራ፣

ተጠኝ ተማሪዎች እና የሙከራ ትምህርት መምህር የተመረጡበት የንሞና ዘዴዎች በተከታታይ ይቀርባሉ፡፡

### 3.2.1. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ

ይህ ጥናት የተኪያሄደው በኦሮሚያ ክልል፣ በጅማ ዞን፣ በማና ወረዳ፣ በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ የጥናቱ ቦታ የተመረጠው በአመቺ የንሞና ዘዴ ሲሆን ይህም የተደረገበት ምክንያትም ትምህርት ቤቱ አጥኝዋ በምትኖርበት አካባቢ የሚገኝ በመሆኑ ለጥናቱ የሚያስፈልገውን የጊዜ እና የገንዘብ ወጪ እንደሚቀንስ በመታመኑ ነው፡፡ በተጨማሪም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ትግበራውን ለማከናወን ፈቃደኛ የሆኑ መምህራን በተመረጠው ትምህርት ቤት በመኖራቸው ተገቢውን የጥናት ሂደትና የሙከራ ትምህርት ለማከናወን እንደሚያመች ስለታመነበት ነው፡፡

### 3.2.2. የክፍል ደረጃ የናሙና አመራረጥ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህ ጥናት የተከናወነው በዶዮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ ከተመረጠ በኋላ በ2016 የትምህርት ዓመት በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ 9ኛ ክፍል በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ በጥናቱ የክፍል ደረጃነት ተመርጧል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚጀመሩት ከ9ኛ ክፍል በመሆኑ በዚህ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች የመጻፍ ክሒል እንዲዳብር ክሒሉ አጽንዖት ተሰጥቶት መሰጠት የሚገባበት የክፍል ደረጃ እንደሆነ አጥኝዋ ታምናለች፡፡

በአንጻሩ ደግሞ 10ኛ ክፍል በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ተማሪዎች ለመጨረሻ ዓመት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የሚማሩበት የክፍል ደረጃ ነው፡፡ ማለትም በአካባቢው የሚገኙት ተማሪዎች አፋቸውን የሚፈቱት በአፋን ኦሮሞ በመሆኑና ወደ 11ኛ ክፍል ሲዘዋወሩ በአማርኛ ቋንቋ ምትክ አፋን ኦሮሞን ስለሚመርጡ ከ10ኛ ክፍል በኋላ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን አይማሩም፡፡ በመሆኑም 9ኛ ክፍል ላይ እያሉ ጥሩ የመጻፍ ክሒል ከሌላቸው በ10ኛ ክፍል ደረጃቸው ትምህርቱን በሚገባ የመከታተል ፍላጎት ላይኖራቸው ይችላል፡፡ በጥናቱ የተሰጠውን ትምህርት በሚገባ ካልተከታተሉ ደግሞ በጥናቱ ውጤት ላይ

አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ስለሚችል 9ኛ ክፍል ጥናቱን የተከናወነበት የክፍል ደረጃ ተደርጎ ተመርጧል፡፡

### 3.2.3. የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች አመራረጥ

በትምህርት ቤቱ በ2016 ዓ.ም አራት የ9ኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ ናሙናዎችን ከየክፍሉ ከማውጣት ይልቅ ሁለት ምድቦችን መምረጥ የተሻለ እንደሆነ በአጥኚዋ ታምኖበታል፡፡ ምክንያቱም ከተለያዩ ምድቦች ተማሪዎችን መምረጥ በጥናቱ ትምህርት ሂደት የመረባበሽ ሁኔታ ሊገጥም ከመቻሉም በተጨማሪ ተማሪዎች ባባቸው ምድቦች መመረጣቸው የጥናቱ ትምህርት በትክክለኛው የመማሪያ ክፍል ዓውድ ለማድረግ አመቺ በመሆኑ ነው፡፡

በዚህም መሰረት በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ 4 የ9ኛ ክፍል ምድቦች ውስጥ ሁለቱን በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ በመቀጠልም በሁለቱ ምድቦች መካከል እንደገና እጣ በማውጣት በወጣላቸው እጣ መሰረት አንዱን ምድብ በሙከራ ቡድንነት፣ እንዲሁም ሌላኛውን ምድብ ደግሞ በቁጥጥር ቡድንነት ተመድበው ጥናቱ ተደርጎባቸዋል፡፡ የምድቦቹ አመራረጥ ቀላል የዕጣ ንሞና የሆነበት ምክንያት አራቱም ምድቦች በጥናቱ የመካተት እድል እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡ እንዲሁም በሁለቱ ምድቦች መካከል እንደገና እጣ ማውጣት ያስፈለገው የቡድኖቹ አመዳደብ ከአድሎ የጸዳ እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

### 3.2.4. የመምህር አመራረጥ

ይህ ጥናት ከፊል ሙከራዊ ጥናት እንደመሆኑ የሙከራ ትምህርቱን የሚያስተምር መምህር መመረጥ ነበረበት፡፡ የሚያስፈልገው መምህር አንድ ብቻ ሲሆን ሁለቱም ቡድኖች በተመረጠው አንድ መምህር ተምረዋል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ከመምህሩ የማስተማር ብቃት አንጻር ሊፈጠር የሚችለውን ልዩነት ለማስወገድ ነው፡፡ መምህሩ የተመረጠው በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ነው፡፡ ይህም የተደረገው ከመምህሩ የማስተማር ልምድና የትምህርት ዝግጅት አንጻር የጥናቱን ትምህርት በሚገባ ሊያስተምር የሚችል መምህር ለመምረጥ ይቻል ዘንድ ነው፡፡

በዚህም መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የማስተርስ ዲግሪ ያለውና በመምህርነት የ23 ዓመት ልምድ ያለው መምህር ተመርጧል፡፡ መምህሩ ከተመረጠ በኋላ የጥናቱን ትምህርት

የሚያስተምርበትን መንገድ በተመለከተ የሁለት ሳምንት ስልጠና ተሰጥቶታል፡፡ ከስልጠናው በኋላ በጥናቱ ያልተመረጡ ተማሪዎች ላይ ልምምድ አድርጓል፡፡ በመጨረሻም የጥናቱን ተማሪዎች ለ10 ክፍለ ጊዜዎች ተምረዋል፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገለው መሳሪያ ፈተና ነው፡፡ የፈተናው ዓላማም የጥናቱ ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል መመዘን ነው፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግም ሁለት ፈተናዎች የተዘጋጁ ሲሆን አንዱ ከትምህርቱ በፊት ሌላኛው ደግሞ ከትምህርቱ በኋላ ተሰጥቷል፡፡ ከትምህርቱ በፊት የተሰጠው ቅድመ ፈተና ዓላማው በሁለቱ ቡድን የተካተቱት ተማሪዎች ያላቸው የመጻፍ ክሒል ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ እንዲሁም ከጥናቱ ትምህርት በኋላ የተሰጠው ደግሞ የጥናቱ ትምህርት በተማሪዎቹ የመጻፍ ክሒል ላይ ያመጣውን ለውጥ ማረጋገጥ ነው፡፡

ፈተናው የተዘጋጀው በአጥኚዋ ሲሆን ከተዘጋጀ በኋላ ልምድ ባላቸው መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ተገምግሟል፡፡ በግምገማው ወቅት የተሰጠውን አስተያየት መሰረት በማድረግ እንደገና ተስተካክለዋል፡፡ በመቀጠልም በጥናቱ ያልተካተቱ 30 ተማሪዎችን በመምረጥ ፈተናውን እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ ይህም የተደረገው የፈተናውን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ሲሆን ፈተናውን ከተፈተኑ በኋላ በክሮምባች አልፋ ተሰልቷል፡ ፡ የክሮምባች አልፋው ውጤት እንደሚያመለክተው አልፋ 0.89 ነው፡፡

የክሮምባች አልፋ ስሌቱ እንደሚያመለክተው ፈተናው 89% አስተማማኝ ነው፡፡ የፈተናው አስተማማኝነት ከተረጋገጠ በኋላ ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች ከጥናቱ ትምህርት በፊት እና ከትምህርቱ በኋላ ተሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም የጽሑፍ ክሒል መመዘኛ መስፈርቶችን በመጠቀም ፈተናው ታርሟል፡፡ ፈተናዎቹ ከታረሙ በኋላም ውጤቱ ተሰብስቦ ለመረጃ ትንተና ተወስዷል፡፡

## 3.4. የማስተማሪያ መሣሪያ አዘገጃጀትና የማስተማር ትግበራ

### 3.4.1. የማስተማሪያ መሣሪያ አዘገጃጀት

ይህ ጥናት ከፊል ሙከራዊ ጥናት እንደመሆኑ ለጥናቱ ትምህርት ማስተማሪያነት የሚሆን መሳሪያ መዘጋጀት ነበረበት፡፡ ስለሆነም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተማሩበት ማስተማሪያ አጫጭርማ መካከለኛ ርዝመት ያላቸውን ግጥች በመውሰድ ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተማሩባቸው ማስተማሪያዎች ከ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ተወስደዋል፡፡ በዚህ መንገድ ከተዘጋጁ በኋላ የተመረጡት ተማሪዎች ተምረውባቸዋል፡፡

### 3.4.2 የመማር ማስተማር ተግባር

የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ከላይ በተገለጸው መንገድ ከተዘጋጁ በኋላ ልምድ ባላቸው መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ተገምግመዋል፡፡ ከተገመገሙ በኋላም በግምገማው የተሰጡትን አስተያየቶች መሰረት በማድረግ ተስተካክለው ለማስተማሪያነት ዝግጁ ተደርገዋል፡፡ በመቀጠልም ተጠኚዎቹ ተማሪዎች ከመማራቸው በፊት 30 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተመርጠው የሙከራ ትምህርት ለሁለት ሳምንታት ተሰጥቷል፡፡

በቅድሚያ ለጥናቱ የተመረጠው መምህር ትምህርቱን የሚሰጥበትን መንገድ የተመለከተ የሁለት ሳምንት ስልጠና በአጥኚዋ ተሰጥቷል፡፡ ስልጠናው የተሰጠውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን ለማስተማር ግጥምን፣ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎችን ለማስተማር ደግሞ በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡትን ማስተማሪያዎች እንዲጠቀም ግንዛቤ ተሰጥቶታል፡፡ በመቀጠልም የጥናቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመሩ በፊት በተመረጡት 30 ተማሪዎች እንዲለማመድ ተደርጓል፡፡ በልምምዱ ወቅትም አጥኚዋ ምልከታ በማድረግ የማስተካከያ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡ መምህሩ የጥናቱን ትምህርት ለመስጠት በሚያስችል ደረጃ ብቁ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የጥናቱን ተማሪዎች እንዲያስተምር ተደርጓል፡፡ የጥናቱን ትምህርት ሲያስተምርም አጥኚዋ ምልከታ በማድረግ መስተካከል ያሉባቸው ጉዳዮች እየተስተካከሉ እንዲያስተምር ተደርጓል፡፡

## 3.5. የጥናቱ አሰራር ቅደም ተከተል

በዚህ ጥናት የጥናቱን ዓላማዎች መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የመጀመሪያው ተግባር ከጥናቱ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተዛማጅ ጽሑፎች በጥልቀት መቃኘት ነበር፡፡ በዚህ ሂደትም የጥናቱ ዓላማ ላይ የተመሰረቱ ልዩ ልዩ ጥናቶች በጥልቀት ተመርምረዋል፡፡ በመቀጠል የተከናወነው በመጻፍ ትምህርት ሂደት የግጥም አቀራረብ ምን ይመስላል? የሚለውን የምሁራን ንድፈ ሀሳባዊ እይታን መፈተሽ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ምሁራን የመጻፍ ትምህርት በግጥም አማካኝነት ጽህፈትን ማስተማር ዘዴ እንዴት ይቅረብ? የሚለውን በተመለከተ ልዩ ልዩ ሀሳቦችን አስቀምጠዋል፡፡ የተከናወነው ጥናት ከፊል ሙከራዊ እንደመሆኑ መጠን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ተዘጋጅተው ተግባር ላይ ውለዋል፡፡

ከዚህ አንጻር የጥናቱ መረጃ የመሰብሰቢያ መሳሪያ ፈተና ሲሆን ለቅድመ እና ለድኅረ ፈተና ሊሆኑ የሚችሉ ጥያቄዎች በአጥኚዋ ተዘጋጅተዋል፡፡ ፈተናዎቹ ከተዘጋጁ በኋላ ተገቢነታቸው ልምድ ባላቸው መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ተገምግመው ተስተካክለዋል፡፡ እንዲሁም ፈተናዎቹ አስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በጥናቱ ያልተካተቱ 30 ተማሪዎች ተመርጠው ተፈትነውት የተገኘው ውጤት በክሮምባች አልፋ ተተንትኗል፡፡ በትንተናው መሰረት ፈተናዎቹ አስተማማኝ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች ተፈትነዋቸዋል፡፡ ከፈተናዎቹ የተገኙት መረጃዎችም በባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡

ሌላው በጥናቱ የተከናወነው ተግባር የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች ግጥምን በመጠቀም የተዘጋጀ ሲሆን ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ማስተማሪያዎች በመውሰድ ለማስተማሪያነት አገልግለዋል፡፡ የጥናቱ ተግባራት በዚህ መንገድ ከተከናወኑ በኋላ ጥናታዊ ጽሑፉ ተዘጋጅቷል፡፡

## 3.6. የመረጃ አተናተን

ቀደም ባሉት ክፍሎች ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህን ጥናት ዓላማዎች ማሳካት ይቻል ዘንድ ቅድመ ፈተና እና ድህረ ፈተና ለሁለቱም ቡድኖች ተሰጥቷል፡፡ ፈተናዎቹም

በጥናቱ ላይ ምንም ተሳትፎ በሌላቸውና የአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ልምድ ባላቸው ሶስት መምህራን እንዲታረም ተደርጓል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት በፈተና ማረም ሂደት ሊፈጠር የሚችልን አድሎ ለመቀነስ ነው፡፡ ሶስቱ አራሚዎች ፈተናዎቹን ካረሙቸው በኋላ የሰጡትን ውጤት አማካይ በመውሰድ የመረጃ ትንተና ተደርጓል፡፡

የጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰቡት በፈተናዎች እንደመሆኑ መጠናዊ መረጃዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም መረጃዎቹ የተነተኑት በመጠናዊ የመረጃዎች መተንተኛ ዘዴ (quantitative data analysis method) ነው፡፡ ከመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ውስጥም ነጻ የናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent sample t-test) እና ነጠላ የናሙና ቲ-ቴስት (one sample t-test) በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ሁለቱ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች የየራሳቸው ዓላማዎች አሏቸው፡፡ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎቹ ዓላማ ሶስቱ የጥናቱን ዝርዝር ዓላማዎች ማሳካት የሚችሉ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ነጻ የናሙናዎች ቲ-ቴስትን መጠቀም ያስፈለገው የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቧቸው ፈተናዎች ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡ እንዲሁም ነጠላ የናሙና ቲ-ቴስትን መጠቀም ያስፈለገው ደግሞ የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች በተናጠል ከቅድመ ፈተናው እና ከድህረ ፈተናው ባስመዘገቡት ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡

በዚህ መሰረት የመረጃ ትንተናው በአራት ክፍሎች ተተንትነዋል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች በቅድመ ፈተናው ባስመዘገቡት ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ያገለገለው ነጻ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ተከናውኗል፡፡ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የድህረ ትምህርት ፈተና መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩ ተመርምሯል፡፡ በሶስተኛው ክፍል ደግሞ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ፈተና እና የድህረ ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ያገለገለው ነጠላ የናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ተከናውኗል፡፡ በመጨረሻም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ፈተና እና የድህረ ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ያገለገለው ነጠላ የናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ተከናውኗል፡፡

## 3.7. የጥናቱ ሥነ ምግባራዊ ሁኔታ

የጥናቱን ሥነ ምግባራዊ ሁኔታ ለመጠበቅ አጥኚዋ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ጥረት አድርጋለች፡፡ የመጀመሪያው ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች ስለጥናቱ ዓላማ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ በግንዛቤ ማስጨበጫ ሂደቱም ተማሪዎች ከመደበኛ የትምህርት ክፍለ ጊዜያቸው በተጨማሪ የመጻፍ ትምህርት እንደሚማሩ የማሳወቅ ሥራ በአጥኚዋ እና በተመረጠው የአማርኛ ቋንቋ መምህር በኩል ገለጻ ተደርጎላቸዋል፡፡ እንዲሁም የሚያከናውኗቸውን ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራት ለጥናቱ ዓላማ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው በመጠቆም በመጨረሻ መስማማታቸውን የሚገልጽ የስምምነት ውል እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተፈተኑት ቅድመ እና ድኅረ ፈተና እንዲሁም በእያንዳንዱ የመጻፍ ተግባር የሚያስመዘግቡት ውጤት ማንነታቸው ሳይገለጽ በኮድ ስማቸው ሰፍሯል፡፡ ጥናቱ ተከናውኖ ካለቀ በኋላ የተገኘውን ውጤት ጥናቱ ለተከናወነበት ትምህርት ቤት አጥኚዋ አሳውቃለች፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1. የጥናቱ የመረጃ ትንተና

ይህ ጥናት ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽዖ ለመፈተሽ ነው፡፡ ለዚህም ሁለት መላምቶች ተሰንዝረው አንዱ ተቀባይነት ሲያገኝ ሌላኛው ደግሞ ውድቅ ተደርጓል፡፡ መላምቶቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በጉልህ አያሳድግም (አልቦ መላምት)፤
- ✓ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በጉልህ ያሳድጋል (አማራጭ መላምት)

እነዚህን ሁለት መላምቶች በመፈተሽ አንዱን ውድቅ ተደርጎ ሌላኛው ተቀባይነት እንዲያገኝ ሁለት የ9ኛ ክፍል ምድቦች ተመርጠው ከፊል ሙከራዊ ጥናት ተከናውኖባቸዋል፡፡ ለጥናቱ ያገለገሉት መረጃዎችም በፈተና የተሰበሰቡ ሲሆን የመረጃዎቹ አይነትም መጠናዊ መረጃዎች ናቸው፡፡ ቀጥሎ በጥናቱ የተሰበሰቡት መረጃዎች በተገቢዎቹ የመተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡

### 4.1.1. የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከጥናቱ ትምህርት በፊት ያላቸው የመጻፍ ክሂል

በምዕራፍ ሶስት እንደተገለጸው ጥናቱ የተደረገባቸው ሁለት የ9ኛ ክፍል ምድቦች ተመርጠዋል፡፡ ሁለቱ ምድቦች ከተመረጡ በኋላ የጥናቱ ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት የቅድመ ትምህርት ፈተና ለሁለቱም ቡድን ተማሪዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡ የቅድመ ትምህርት ፈተና መስጠት ያስፈለገውም ከጥናቱ ትምህርት በፊት በሁለቱ ቡድን ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች ያላቸው የመጻፍ ክሂል ተቀራራቢ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የቅድመ ትምህርት ፈተናው ለተመረጡት ሁለት የ9ኛ ክፍል ምድቦች ከተሰጠ በኋላ

በጥናቱ ምን አይነት ተሳትፎ የሌላቸው ሶስት መምህራን ተመርጠው እንዲያርሙ ተደርጓል፡፡ ለማረም ያገለገሉ መስፈርቶችም ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሶስቱ አራሚዎች ፈተናውን እንዲያርሙት ተደርጎ አስተራረሙ አስተማማኝ መሆን አለመሆኑ በክሮምባች አልፋ ተሰልቷል፡፡ ከስሌቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያለክተውም የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርት ፈተና የክሮምባች አልፋ ውጤት 0.980 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርት ፈተና ክሮምባች አልፋ ደግሞ 0.974 ሆኗል፡፡ በዚህም የሙከራ ቡድን እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና አስተራረም በተከታታይ 98% እና 97% አስተማማኝ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የአስተራረሙ አስተማማኝነት ከተረጋገጠ በኋላም የሶስቱን አራሚዎች አማካይ በመውሰድ የመረጃ ትንተናው ተከናውኗል፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ሰንጠረዥ የሚያመለክተው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ነጻ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ነው፡፡

*ሰንጠረዥ 4.1፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና*

| **ቡድኖች** (groups) | **ናሙና** (sample) | **አማካይ ውጤት** (M) | **መደበኛ ልይይት** (SD) | **የአማካይ ልዩነት** (mean difference) | **የቲ ዋጋ** (t-value) | **የነጻነት ደረጃ** (Df) | **ባለ 2 ጫፍ ጉልህነት** (P) | **ጉልህ ልዩነት** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የሙከራ ቡድን** | 35 | 44.886 | 10.16 | 3.37 | 1.341 | 68 | .184* | **የለም** |
| **የቁጥጥር ቡድን** | 35 | 41.514 | 10.86 | | | | | |

*P>0.05

በሰንጠረዥ 4.1 የቀረበው ትንተና የተከናወነው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡትን ውጤት በመውሰድ ሲሆን ይህም የጥናቱ ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ያላቸው የመጻፍ ክሒል ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ አገልግሏል፡፡ በሰንጠረዡ የቀረበው ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተናው እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት 44.886 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 10.16 ነው፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት 41.514 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 10.86 ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት መካከል የ3.37 ልዩነት እንዳለ ሲሆን የሚበልጠውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት ነው፡፡

ያለው (2006) እንደሚገልጹት የሁለት ቡድኖችን አማካይ ውጤት በመውሰድ ብቻ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ይህንን ማረጋገጥ የሚቻለው የባለሁለት ጫፍ ጉልህነቱንና የ‹ቲ›ን ዋጋ በመውሰድ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የባለሁለት ጫፍ ጉልህነቱ (P) የጉልህነት መወሰኛ ከሆነው 0.05 የሚያንስ ከሆነ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የውጤት ልዩነት እንዳለና የሚበልጥ ከሆነ ደግሞ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት እንደሌለ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም የ‹ቲ› ዋጋ የቲ ሰንጠረዥ ዋጋ ከሆነው 2.00 የሚበልጥ ከሆነ በቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት እንዳለና የሚያንስ ከሆነ ደግሞ ጉልህ ልዩነት እንደሌለ ያመለክታል፡፡ ከእነዚህ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ የሚጓደል ከሆነ የትንተናው ውጤት ትአማኒነት እንደማይኖረው ያለው (2006) ጨምረው ያስረዳሉ፡፡

ቀደም ሲል በሰንጠረዥ 4.1 የቀረበው የባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና እንደሚያሳየው ባለሁለት ጫፍ ጉልህነቱ (P) 0.184 ሲሆን ይህም የጉልህነት መወሰኛ ከሆነው 0.05 ይበልጣል፡፡ እንዲሁም የ‹ቲ› ዋጋ ደግሞ 1.341 ሲሆን ይህም የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከሆነው 2.00 ያንሳል፡፡ ይህ የባዕድ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና የሚያመለክተውም ምንም እንኳን የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት በ3.37 ቢበልጥም ብልጫው ግን ጉልህ እንዳልሆነ ነው፡፡

በሙከራ ቡድን ተማሪዎችና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩ የሚያመለክተው የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ያላቸው የመጻፍ ክሒል ተመጣጣኝ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የጥናቱን ትምህርት ለማከናወን ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ የተመረጡት የመጻፍ ክሒል ትምህርቶች ለሁለቱ ምድብ ተማሪዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡ የጥናቱ ትምህርት የተሰጠውም በተለያዩ ማስተማሪያዎች ሲሆን ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች ግጥምን በመጠቀም፣ እንዲሁም ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ማስተማሪያዎች በመጠቀም ትምህርቱ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የጥናቱ ትምህርት ተሰጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላም የሁለቱም ቡድን ተማሪዎች የድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይህንን ማድረግ ያስፈለገውም የጥናቱ ትምህርት በተማሪዎቹ የመጻፍ ክሒል ላይ ጉልህ

መሻሻል ማምጣት አለማምጣቱን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ከድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኙት መረጃዎችም ቀጥሎ ተተንትነዋል፡፡

### 4.1.2. የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ከጥናቱ ትምህርት ያስመዘገቡት ውጤት

ከላይ የቀረበው ትንተና እንደሚያመለክተው የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የጥናቱን ትምህርት ከመማራቸው በፊት ባስመዘገቡት የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት የለም፡፡ ትምህርቱን ከተማሩ በኋላም የድህረ ትምህርት ፈተና ለሁለቱም ቡድን ተማሪዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡ በመቀጠል የጥናቱ ትምህርት በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ጉልህ መሻሻል ማምጣት አለማምጣቱን ለማረጋገጥ የተማሪዎቹ የቅድመ ትምህርት ፈተና እና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ተወስዶ ተተንትኗል፡፡

***ሰንጠረዥ 4.2፡- የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ነጠላ የናሙና ቲ-ቴስት ትንተና***

| **ፈተናዎች** (tests) | **ናሙና** (sample) | **አማካይ ውጤት** (M) | **መደበኛ ልይይት** (SD) | **የአማካይ ልዩነት** (mean difference | **የቲ ዋጋ** (t-value) | **የነጻነት ደረጃ** (Df) | **ባለ 2 ጫፍ ጉልህነት** (P) | **ጉልህ ልዩነት** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቅድመ ፈተና** | 35 | 41.514 | 10.86 | | | | | |
| **ድህረ ፈተና** | 35 | 43.286 | 10.48 | -1.771 | -.694 | 68 | .490* | **የለም** |

*P>0.05

የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ጉልህ መሻሻል ማሳየት አለማሳየታቸውን ለማረጋገጥ ተማሪዎቹ ከቅድመ ትምህርት ፈተና እና ከድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት ውጤት ተወስዶ ከላይ በቀረበው የነጠላ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ተተንትኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው እንደሚያመለክተው የቅድመ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት 41.514 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 10.86 ነው፡፡ እንዲሁም የድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት 43.286 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 10.48 ነው፡፡ በሁለቱ ፈተናዎች አማካይ መካከል ያለው የውጤት ልዩነት -1.771 ሲሆን የኔጌቲቭ ምልክቱ የሚያመለክተው የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቱ ከቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤቱ እንደሚበልጥ ነው፡፡

ቀደም ባለው ክፍል እንደተገለጸው በሁለት ናሙናዎች መካከል የሚታየው የአማካይ ውጤት መበላለጥ ብቻውን ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን አያመለክትም፡፡ በተማሪዎቹ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት እና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተናው የቀረበውን የጉልህነት ደረጃ እና የቲ-ዋጋ መመርመር ተገቢ ነው፡፡ በሰንጠረዥ 4.2 የቀረበው የጉልህነት ደረጃ (P) 0.490 ሲሆን የ‹T› ዋጋ ደግሞ -.694 ነው፡፡ ይህ ትንተና የሚያመለክተውም የጉልህነት ደረጃው የጉልህነት ደረጃ መወሰኛ ከሆነው 0.05 እንደሚበልጥና የቲ ዋጋ ደግሞ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከሆነው 2.00 እንደሚንስ ነው፡፡ ይህ ትንተና የሚያመለክተውም ምንም እንኳን የተማሪዎቹ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት ቢበልጥም ብልጫው ጉልህ አለመሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ውጤት በመነሳትም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተማሩበት በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት ማስተማሪያዎች በተማሪዎቹ የመጻፍ ክሒል መሻሻል ላይ ጉልህ ለውጥ ማምጣት እንዳልቻለ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.1.3. የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ያስመዘገቡት ውጤት

የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የጥናቱን ትምህርት የተማሩት ግጥምን በመጠቀም ነው፡፡ ይህም የተደረገው በግጥም መማር በተማሪዎቹ የመጻፍ ክሒል ላይ ጉልህ ለውጥ ማምጣት መቻል አለመቻሉን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ትምህርቱን ተምረው ከጨረሱ በኋላ ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ በመቀጠል የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና እና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ተወስዶ የተደረገው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ቀርቧል፡፡

***ሰንጠረዥ 4.3፡- የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ነጠላ የናሙና ቲ-ቴስት ትንተና***

| ፈተናዎች (tests) | ናሙና (sample) | አማካይ ውጤት (M) | መደበኛ ልይይት (SD) | የአማካይ ልዩነት (mean difference) | የቲ ዋጋ (t-value) | የነጻነት ደረጃ (Df) | ባለ 2 ጫፍ ጉልህነት (P) | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ቅድመ ፈተና** | 35 | 44.89 | 10.16 | -10.829 | -4.257 | 68 | .000* | **አለ** |
| **ድህረ ፈተና** | 35 | 55.71 | 11.10 | | | | | |

*P<0.05

በሰንጠረዥ 4.3 የቀረበው ነጠላ የናሙና ቲ-ቴስት ትንተና የተከናወነው የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት እና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት በመውሰድ ነው፡፡ ይህንን ትንተና ማድረግ ያስፈለገውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ጉልህ ለውጥ ማምጣት አለማምጣታቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን በዚህም ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎቹን የመጻፍ ክሒል በማሻሻል ረገድ ያለው አስተዋጽዖ ምን ያህል እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሰንጠረገፉ የቀረበው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 44.89 ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ደግሞ 55.71 ነው፡፡ እንዲሁም የቅድመ ትምህርት ፈተናው መደበኛ ልይይት 10.16 ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተናው መደበኛ ልይይት ደግሞ 11.10 ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው የተማሪዎቹ የቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት ከድህረ ትምህርት ፈተናው ውጤት በ10.829 እንደሚያንስ ነው፡፡ የድህረ ትምህርት ፈተናው ውጤት የቅድመ ትምህርት ፈተናውን ውጤት ይብለጥ እንጂ ብልጫ መኖሩ ብቻውን በሁለቱ ፈተናዎች መካከል ያለው ልዩነት ጉልህ መሆን አለመሆኑን አያመለክትም፡፡ የሁለቱ ፈተናዎች ውጤት ጉልህ ልዩነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ የትንተናውን የጉልህነት ደረጃ (P) እና የ‹T› ዋጋ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በሰንጠረገፉ የቀረበው የጉልህነት ደረጃ (P) 0.000 ሲሆን የ‹T› ዋጋ ደግሞ -4.257 ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው የጉልህነት ደረጃው (P) የጉልህነት ደረጃ መወሰኛ ከሆነው 0.05 እንደሚያንስና የ‹T› ዋጋ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከሆነው 2.00 እንደሚበልጥ ነው፡፡

ከላይ የቀረበው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተናው የጉልህነት ደረጃ እና የቲ-ዋጋ የሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት እና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ሲሆን የሚበልጠውም የተማሪዎቹ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ጉልህ መሻሻል እንዳመጡ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎቹ የተማሩበት ግጥምን በማስተማሪያነት መጠቀም የተማሪዎቹን የመጻፍ ክሒል በጉልህ ማሻሻል እንደሚችል ነው፡፡

### 4.1.4. ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር ለተማሪዎች የመጻፍ ክሒል ማደግ ያለው ሚና

ከላይ የቀረቡት ሶስት የመረጃ ትንተናዎች እንደሚያሳዩት ከጥናቱ ትምህርት በፊት በተፈተኑት የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ተቀራራቢ ውጤት ነበራቸው፡፡ ይህ ከተረጋገጠ በኋላም የጥናቱ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ ትምህርቱ የተሰጠው በተለያዩ የማስተማሪያዎች ሲሆን የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ግጥምን በመጠቀም፣ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ በመማሪያ መጽሐፉ ያሉትን ማስተማሪያዎች በመጠቀም ተምረዋል፡፡ ትምህርቱ ተሰጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላ የሁለቱም ቡድን ተማሪዎች አንድ አይነት የድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ በመቀጠል የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ያስመዘገቡት የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ተወስዶ በነጻ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ተተንትኗል፡፡

***ሰንጠረዥ 4.4፡- የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ነጻ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና***

| ቡድኖች (groups) | ናሙና (sample) | አማካይ ውጤት (M) | መደበኛ ልይይት (SD) | የአማካይ ልዩነት (mean difference | የቲ ዋጋ (t-value) | የነጻነት ደረጃ (Df) | ባለ 2 ጫፍ ጉልህነት (P) | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የሙከራ ቡድን** | 35 | 55.714 | 11.10 | | | | | |
| **የቁጥጥር ቡድን** | 35 | 43.29 | 10.48 | 12.429 | 4.817 | 68 | .000* | **አለ** |

*P<0.05

በሰንጠረዥ 4.4 የቀረበው ነጻ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና የተከናወነው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ከድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡትን ውጤት በመውሰድ ነው፡፡ ይህንን ትንተና ማድረግ ያስፈለገውም የጥናቱ ትምህርት በተማሪዎቹ የድህረ ትምህርት ውጤት ላይ ያመጣውን መሻሻል ለማረጋገጥ ሲሆን በዚህም የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከተማሩባቸው ማስተማሪያዎች የትኛው የበለጠ ውጤታቸውን እንዳሻሻለ ለማረጋገጥ በጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በሰንጠረዥ 4.4 የቀረበው ባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት 55.714 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት ደግሞ 43.29 ነው፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች መደበኛ ልይይት 11.1 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መደበኛ ልይይት ደግሞ 10.48 ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት በ12.43 እንደሚበልጥ ነው፡፡

በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት መካከል ልዩነት መኖሩ ብቻውን በቡድኖቹ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አያመለክትም፡፡ በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ የትንተናውን የጉልህነት ደረጃ (P) እና የ‹T› ዋጋ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ በሰንጠረዡ የቀረበው የጉልህነት ደረጃ (P) 0.000 ሲሆን የ‹T› ዋጋ ደግሞ 4.817 ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው የጉልህነት ደረጃው (P) የጉልህነት ደረጃ መወሰኛ ከሆነው 0.05 እንደሚያንስና የ‹T› ዋጋ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ከሆነው 2.00 እንደሚበልጥ ነው፡፡ ይህም የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተናው የጉልህነት ደረጃ እና የቲ-ዋጋ የሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ያስመዘገቡት የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎችን የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በጉልህ እንደሚበልጥ ነው፡፡

## 4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ያለውን አስተዋፅኦ መመርመር ነው፡፡ ይህ ዓቢይ ዓላማም ሶስት ዝርዝር ዓላማዎችን ያካተተ ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹን መሰረት ያደረጉ ሶስት ጥያቄዎች ተዘጋጅተው በተደረገው ከፊል ሙከራዊ ጥናት ጥያቄዎቹ መልስ አግኝተዋል፡፡ ለጥናቱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በተደረገው ከፊል ሙከራዊ ጥናት ለጥናቱ የተመረጡት የሁለት ምድብ ተማሪዎች በቅድሚያ ቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸው የተገኘው ውጤት በነጻ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ተተንትኗል፡፡ የቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት ተወስዶ የተደረገው የመረጃ ትንተና እንዳመለከተው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአማካይ ውጤት ልዩነት የለም (P>0.05)፡፡ በመቀጠልም የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን ግጥምን በመጠቀም፣ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ማስተማሪያዎች በመጠቀም የጥናቱ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ ትምህርቱ ከተጠናቀቀ በኋላም የድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትነው ያስመዘገቡት ውጤት የጥናቱን ዝርዝር ዓላማዎች መሰረት በማድረግ ተተንትነዋል፡፡ የተደረገው የመረጃ ትንተና የሚያመለክተው ውጤት ደግሞ በዚህ ክፍል እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ጥናቱ ሶስት ዝርዝር ዓላማዎች ሲኖሩት የመረጃ ትንተናው የተከናወነውም ዝርዝር ዓላማዎቹን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የመጀመሪያው የጥናቱ

ዝርዝር ዓላማ ‹‹የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ›› የሚል ነው፡፡ ይህንን ዝርዝር ዓላማ ከግብ ለማድረስም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ከቅድመ ትምህርት ፈተናውና ከድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡትን ውጤት በመውሰድ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ተከናውኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው እንዳመለከተው የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ከድህረ ሙከራ ፈተናው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት በቅድመ ሙከራ ፈተናው ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት በ1.771 ይበልጣል፡፡ ሆኖም ግን ብልጫው ጉልህ አለመሆኑን የባለሁለት ጫፍ ጉልህነቱ (P) ያመለክታል (P = 0.49 > 0.05)፡፡ በዚህም የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተማሩባቸው በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት ማስተማሪያዎች የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል እንደማይችል ተረጋግጧል፡፡

የጥናቱ ሁለተኛ ዝርዝር ዓላማ ‹‹የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መፈተሽ›› የሚል ነው፡፡ ይህንን ዝርዝር ዓላማ ከግብ ለማድረስም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቅድመ ትምህርት ፈተናውና ከድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡትን ውጤት በመውሰድ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ተከናውኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው እንዳመለከተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከድህረ ሙከራ ፈተናው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት በቅድመ ሙከራ ፈተናው ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት በ9.36 ይበልጣል፡፡ በተጨማሪም ብልጫው ጉልህ መሆኑን የባለሁለት ጫፍ ጉልህነቱ (P) እና የ‹ቲ› ዋጋ ያመለክታሉ (P = 0.000 > 0.05፤ T = -4.257 > 2.00)፡፡ በዚህ የመረጃ ትንተና ውጤት መሰረትም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተማሩበት ግጥምን በመጠቀም ማስተማር የተማሪዎችን ውጤት በጉልህ ማሻሻል እንደሚችል ተረጋግጧል፡፡

የመጨረሻው የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ‹‹ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሒል ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ›› የሚል ነው፡፡ ይህንን ዝርዝር ዓላማ ለማሳካትም የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ከድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት ውጤት ተወስዶ በባዕድ የናሙናዎች ቲ-ቴስት ትንተና ተተንትኗል፡፡ የመረጃ ትንተናው እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ

ውጤት በ6.667 ይበልጣል፡፡ ይህ የአማካይ ውጤት ብልጫ ጉልህ እንደሆነም ባለሁለት ጫፍ ጉልህነቱ (P) እና የ‹ቲ› ዋጋ ያመለክታሉ (P = 0.000 < 0.05፣ T = 4.817 > 2.00)፡፡ ከዚህ ውጤት በመነሳትም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተማሩበት ግጥምን በመጠቀም ማስተማር የተማሪዎቹን ውጤት በማሳደግ ረገድ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳለው ተረጋግጧል፡፡

ከላይ የተገኙት የዚህ ጥናት ውጤቶች በዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ላይ በተሰሩት ተዛማጅ ጥናቶች ከተገኙት ውጤቶች ጋር የሚስማሙ ናቸው፡፡ በምዕራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው አጥኚዋ ባደረገችው የጥናት ቅኝት ስነ ጽሑፍን በመቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ላይ ያደረገ የአማርኛ ቋንቋ ጥናት አላጋጠማትም፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥናት ትኩረት ካደረገበት የስነ ጽሑፍ ዘርፍ እና ከቋንቋ ክሒል አንጻር በጥናቶቹ ያልተዳሰሱ ጉዳዮች በዚህ ጥናት ተዳስሰው የጥናቶቹ ክፍተቶች ተሞልተዋል፡፡

በምዕራፍ ሁለት የተቃኙት ሶስት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱ ጥናቶች ሲሆኑ ጥናቶቹም ገሊላ (2010)፣ ታዛነህ (2012) እና ፍሬሕይወት (2014) ናቸው፡፡ ሶስቱም ጥናቶች የተከናወኑት ስነ ጽሑፍን በቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ መመርመር ላይ ትኩረት አድርገው ነው፡፡ ጥናቶቹ እንደሚያመለክቱት ስነ ጽሑፍን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጉልህ ያሳድጋል፡፡ በዚህ ጥናት ደግሞ በሶስቱም ጥናቶች ተነጥሎ ያልተመረመረው ግጥም በማስተማሪያነት በጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በውጤቱም ግጥም የተማሪዎችን የመጻፍ ክሒል በጉልህ ማሳደግ ይችላል፡፡ በዚህም ግጥምን በማስተማሪያነት መጠቀም ከቋንቋ ክሒሎች አንጻር ሰፊ ዓውድ እንዲኖረው ማድረግ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች

## 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሒል ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ የመረመረ ጥናት ነው፡፡ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ፈተና የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ በመሆን አገልግሏል፡፡ ፈተናን በመጠቀም የተሰበሰበው መረጃ በመጠናዊ መተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡

በመጀመሪያ የታየው የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ያላቸውን አማካይ ውጤት ነው፡፡ ውጤቱ የሚያመለክተውም በሁለቱ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች ከልምምድ በፊት የመጻፍ ችሎታቸው ተቀራራቢ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን ነው፡፡ ልዩነታቸውም በስታስቲክስ ስሌት ተሰልቶ የተገኘው ውጤቱ የቲ ዋጋ (1.341) የP ዋጋ (0.184) አሳይቷል፡፡ ይህም በመጻፍ ችሎታ ረገድ በሁለቱም ቡድኖች አማካዮች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም የ P ዋጋ ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) በልጦ ተገኝቷል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች በቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ካስመዘገቡት ውጤት በመነሳት ተቀራራቢ ደረጃ ላይ እንዳሉ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በድህረ ፈተና ደግሞ ሁለቱ ቡድኖች ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት መገንዘብ እንደሚቻለው የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተና ያስመዘገበው አማካይ ውጤት ብልጫ ማሳየቱን ነው፡፡ ልዩነታቸውም በስታስቲክስ ስሌት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የቲ ዋጋ (4.817) የP ዋጋ (0.000) ሆኗል፡፡ ይህም በቡድኖች መካከል ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም የP ዋጋ (0.000) ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንሶ በመገኘቱ ነው፡፡ ይህ ውጤት የሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ የመጻፍ ችሎታ ውጤት የተሻለ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተን ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን ውጤት ከማሻሻል አንፃር ጉልህ አስተዋፅዖ እንዳለው ነው፡፡

ሌላው የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ እና የድህረ ትምህርት የመጻፍ ፈተና ሲሆን አማካይ ውጤቱ (41.514) እንደሚያሳየው የድህረ ትምህርት የመጻፍ ፈተና አማካይ (43.286) የ1.771 ብልጫ እንዳለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ብልጫው ጉልህ እንዳልሆነ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተናው ያመለክታል፡፡ ይህም የሚያመለክተው በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት ማስተማሪያዎች የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ እንደሌለው ነው፡፡

የሙከራ ቡድኑ ደግሞ በቅድመ እና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ፈተና አማካይ ውጤቱ እንደሚያሳየው የድህረ ትምህርት የመጻፍ ፈተና ጉልህ ልዩነት እንዳለው ነው፡፡ የስታቲስቲክስ ስሌቱ እንደሚያሳየው በ68 የነፃነት ደረጃ የቲ ዋጋ (4.257) የፒ-ዋጋ (0.000) ከመቁረጫው ነጥብ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱም አማካዩች መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ለውጡ የመጣው ከጥናቱ ትምህርት በኋላ በመሆኑ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሒል የሚያሳድግ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

## 5.2 መደምደምያ

ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረውን አስተዋፅኦ መፈተሽን አላማ አድርጎ የተነሳው ይህ ጥናት ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማርና በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ማስተማሪያዎች በመጠቀም ባደረገው ፍትነታዊ ሙከራ መረጃዎችን በፈተና በመሰብሰብ ነጠላ የናሙና ቲ-ቴስትን እና ነጻ የናሙና ቲ-ቴስትን በመጠቀም በመተንተን የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ የሚከተሉት መደምደምያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

- ✓ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሒል ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽዖ አለው፡፡
- ✓ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት የለም፡፡
- ✓ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ባስመዘገቡት የቅድመ ትምህርት ፈተና እና በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለ፡፡

## 5.3. የመፍትሄ ሐሳብ

ይህ ጥናት የተከናወነውም ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሒል ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ ለመመርመር ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ በተከናወነው ከፊል ሙከራዊ ጥናት ቀደም ሲል የተገለጹት ውጤቶች ተገኝተው ከላይ ያሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡ በጥናቱ የተደረሰባቸውን መደምደሚያዎች መሰረት በማድረግም የሚከተሉት ስነ ትምህርታዊ አስተያየቶችና የጥናት አቅጣጫዎች ተጠቁመዋል፡፡

### ስነ ትምህርታዊ አስተያየቶች

በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤትና ውጤቱን መሰረት በማድረግ የተሰጠው ድምዳሜ ከላይ ቀርቧል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ለመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የሚከተሉት ስነ ትምህርታዊ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡

- ✓ የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን የመጻፍ ክሒልን ሲያስተምሩ የተለያዩ ግጥሞችን በመምረጥ ተማሪዎቻቸውን ቢያስተምሯቸው የተማሪዎቻቸውን የመጻፍ ክሒል ማዳበር ይችላሉ፡፡

- ✓ በየደረጃው ያሉ የትምህርት ባለሙያዎች ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሒል ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽዖ በተመለከተ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን በየጊዜው የስራ ላይ ስልጠና ቢሰጧቸው መምህራኑ ግንዛቤ በማግኘት ግጥምን በማስተማሪያነት እንደሚጠቀሙበት ይታመናል፡፡

### የጥናት አቅጣጫዎች

ቀድም ሲል የቀረቡት አስተያየቶች የተሰጡት የጥናቱን ውጤት በመመርኮዝ ሲሆን አስተያየቶቹም ስነ ትምህርታዊ ናቸው፡፡ በዚህኛው ክፍል ደግሞ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የሰፋ አንድምታ እንዲኖረው ሌሎች አጥኝዎች ተጨማሪ ጥናቶችን ቢከናወኑ ጥሩ እንደሆነ የሚጠቁሙ አስተያየቶች ይቀርባሉ፡፡

- ✓ ይህ ጥናት የተከናወነው በአፋን ኦሮሞ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ይህም በሌሎች ሀገር በቀል ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ላይ የሚገኘውን

ውጤት ላይወክል ይችላል፡፡ ስለሆነም ሌሎች አጥኝዎች በሌሎች ሀገር በቀል ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ላይ ጥናታቸውን ቢያደርጉ የዚህ ጥናት ዓውድ ይሰፋል፡፡

- ✓ ይህ ጥናት ግጥምን ብቻ በመነጠል የተከናወነ ጥናት ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ውጤት የሌሎችን የስነ ጽሑፍ ዘርፎች ውጤት ላይወክል ይችላል፡፡ ስለሆነም ሌሎች አጥኚዎች ሌሎች የስነ ጽሑፍ ዘርፎችን ነጥለው ቢያጠኑ የስነ ጽሑፍ ዘርፎች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ያለውን ፋይዳ የተመለከተ ከዚህ የሰፋ ግንዛቤ ይገኛል፡፡

- ✓ ይህ ጥናት የተሞከረው በመጻፍ ክሒል ችሎታ ላይ ብቻ ሲሆን የጥናቱ ውጤት ሌሎች ክሒሎችን ላይወክል ይችላል፡፡ ስለሆነም ሌሎች አጥኚዎች ግጥም ሌሎች የቋንቋ ክሒሎችን ለማሳደግ ያለውን ሚና በጥናት ቢያረጋግጡ የጥናቱ ውጤት ከክሒሎች አንጻር ሰፊ ዓውድ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


መሠረት ጋሊ፡፡ (2013 ዓ.ም)፡፡ *በግጥም አማካኝነት የማንበብ ክሂልን ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ያለው ሚና መፈተሽ*፡፡ በቀርሳ ወረዳ ለምለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)፡፡

ሰለሞን ደኑ፡፡ (2003 ዓ.ም)፡፡ *ልቦለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ*፡ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍሎች መማሪያ መጻህፍት ማሳያነት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)፡፡

በላይነሽ ደነቀ፡፡ (2010 ዓ.ም)፡፡ *የቃላት መምህር ብልሀት በማለት ማሰልጠን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ያለው አስተዋፅኦ ያተኮረ ሙከራዊ ጥናት*፡፡ በዘጠነኛ ክፍል የኦሮምኛ አፈፊት ተማሪዎች) ተተኳሪነት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

በዕውቀቱ ስዩም፡፡ (2001 ዓ.ም)፡፡ ስብስብ ግጥሞች፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት፡፡

ቤት፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ታዛነህ ጋሻው፡፡ (2012)፡፡ *ስነ-ፅሁፋዊና ኢስነ-ፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማሻሻል ረገድ ያላቸው ሚና* (በአዴት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርትቤት በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት)፡፡ በወሊጋ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ነብዩ ጋሹ፡፡ (2005 ዓ.ም)፡፡ *በግጥም አማካኝነት በአማርኛ የአንብቦ መረዳት የፅህፈት ችሎታን ማዳበር በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተካሄደ ሙከራ ጥናት*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)፡፡

አማረ ተሾመ፡፡ (2010 ዓ.ም)፡፡ *ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው ተጽዕኖ*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አዲስ አበባ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992 ዓ.ም)፡፡ የስነፅሁፍ መሰረታዊያን፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ

ገሊላ ክብረት፡፡ (2010)፡፡ ‹‹*ስነ-ፅሁፋዊ እና ስነ-ፅሁፋዊ ያልሆኑ ምንባቦች አንብቦ የመረዳት ክሂልን ከማዳበር አንጻር ያላቸው ሚና (ሙከራዊ ጥናት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)*››፡፡ በደብረ ብርሀን ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ጌትነት አበበ፡፡ (2001 ዓ.ም)፡፡ *በረጅም ልበወለድ ቅንጫቢ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ውጤታማነት የተመረጡ አንድ የምስራቅ ጎጃም ዞን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ላይ ተካሂደ ጥናት*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)፡፡

Ahmad, J. (2014). *Teaching Poetry to Saudi ESL Learners: Stylistic Approach Study in English Language Learning*.

Alamrew G/Mariam. (2005). *A Study on the Perception of Writing, Writing Instruction and Students' Writing Performance*. Addis Ababa University (Unpublished PhD Thesis).

Alexander፣ K. (2017). *Out of Wonder Poems Celeberatig Peets Rnnesata*፣ Caddiueik Pubishing.

Bereiter, C., & Scardamalia, M. (1987). The psychology of written composition. Lawrence Erlbaum Associates.

Byrne,(1997). Teaching Writing Skills. London: Longman Group Ltd.

Byrne,D. (1988). Teaching Writing Skills. Hong Kong: Longman Group Ltd.

Cameron, L. (2003). Metaphor in educational discourse.* Continuum.

Canter፣ Long M.N. (2011). *Teaching Literature*. Uniteed States of America Cong Man

Churchill, K.M., (2013). *Motivating Learning Performance and Persistence*. the Synergetic Effects of Intrinsic Goal Contents and Authonomy supportive context; Journal of Personality and Social Psychology vol 87(2), 246-260

Claros, M.S.C. (2008). *Psycho-Linguistic and Socio-Cultural Approaches to Language Learning*: A never ending debate." Theoretical Discussion Papers, Vol 10, 142-154.

Corford R.L (2004). Language Learning Strategies፡ *What Every Teacher Should Know*. Boston Mn Heininis Heinge.

Ebabu Tefera (2013). *A Study on Writing, Writing: Instruction, Student Perception and Writing Performance*. Addis Ababa University (Unpublished PhD Thesis).

Elbow, P. (1998). Writing with power: Techniques for mastering the writing process. Oxford University Press.

Fleming, M. (1995). *Starting drama teaching.* David Fulton Publishers.

Flower, L., & Hayes, J. R. (1981). A cognitive process theory of writing. College Composition and Communication, 32 (4), 365-387.

Gill. S.R, (2007). *The Forgotten Genres of Children's Poetry*፤ International Reading Association; 10, 622 — 625.

Grainger, T., Goouch, K., & Lambirth, A. (2005). *Creative teaching: Learning with a creative partner.* Routledge.

Graves, D. H. (1983). Writing: Teachers and children at work. Heinemann Educational Books.

Hill, M. & Robert T. (2013). *Criteria for the Selection of Literary Texts*. Oxford University Press.

Hyland, K. (2003). Second language writing. Cambridge University Press.

Mesfin Aberra (2013). *An Explanatory Study on the Implementation of the Process Approach to the teaching Learning of the Course Basic Writing Skills*፡ in the Case of Hawassa University." Addis Ababa University (Unpublished PhD Thesis).

Nunan, D. (1989). *Designing Tasks for the Communicative Classroom*. Cambrigde: cambrigde university press. International journal for infonomics(IJI), volume 13, issue 2, 2020)።

Raimis, A. (1983). *Techniques in the Teaching Writing*. Oxford: Oxford University press.

Richards,J.C.(1974). *Error Analysis Perspectives on Second Language Acquisition*. London and Newyork: Longman Group Ltd.

Silva, T. (1990). *Second Language Composition Instruction:* Developments, Issues, and Directions in ESL. In B. Kroll (Ed.), Second Language Writing: Research Insights for Classroom (pp. 11 — 23) Cambridge: Cambridge University Press.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፤ የመጻፍ ክሂል መመዘኛ ፈተና

### ለጥናቱ የቀረበው የቅድመ እና የድህረ ፈተና

**አጠቃላይ መመሪያ፡- ይህ ፈተና የመጻፍ ክሂልን ለመለካት የተዘጋጀ ነው፡፡ የፈተናው ዋና ዓላማ ግጥምን ተጠቅሞ ማስተማር የጽሕፈት ክሂልን ለማሳደግ ያለው አስተዋጽዖ›› በሚል ርዕስ ለሚከናወነው ጥናት መረጃዎችን መሰብሰብ ሲሆን የፈተናው ውጤት ከዋናው ትምህርት ውጤታችሁ ጋር አይገናኝም፡፡ በፈተናው የተሰጠውን መመሪያ መሰረት አድርጋችሁ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ያላችሁን አጠቃላይ ሀሳብ በተሰጣችሁ ባዶ ወረቀት በመጻፍ መልስ ስጡ፡፡**

**ለፈተናው የተፈቀደ ጊዜ፡-** 2፡00

**ፈተናው የሚጀመርበት ጊዜ፡- ከረፋዱ** 3፡00

**ፈተናው የሚጠናቀቅበት ጊዜ፡- ከረፋዱ** 5፡00

የተማሪ መለያ ኮድ_____________ ምድብ____________ ጾታ_________

ከሚከተሉት የመንደርደሪያ ሀሳቦች ውስጥ አንዱን መርጣችሁ ድርሰት ጻፉ፡፡ ድርሰቱን ከመጻፋችሁ በፊት በድርሰታችሁ ውስጥ የሚነሱ ዋና ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦች የሚያመለክት ቢጋር አዘጋጁ፡፡ በመቀጠልም በቢጋሩ የተነሱ ሀሳቦችን ቅደም ተከተላቸውን በመጠበቅ ድርሰት ጻፉ፡፡ ድርሰታችሁን ስትጽፉ በሚነበብ የእጅ ጽሑፍ ማዘጋጀት የሚጠበቅባችሁ ሲሆን ድርሰታችሁ የሚታረመው ቀጥሎ በቀረቡት መስፈርቶች ነው፡፡

| **መስፈርቶች** | **የያዙት ነጥብ** |
|---|---|
| 1. **የጽሑፍ ይዘት** | 30% |
| 2. **አደረጃጀት** | 20% |
| 3. **ቃላት** | 20% |
| 4. **የቋንቋ አጠቃቀም** | 25% |
| 5. **ሥርዓተ አጻጻፍ** | 5% |

**የመንደርደሪያ ሀሳቦች**

- ✓ በማህበራዊ ሚዲያ ጥቅምና ጉዳት
- ✓ የአየር ንብረት ለውጥ በማህበረሰብ ዘንድ የሚያሳድረው ተፅዕኖ
- ✓ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤ ጥቅሞች
- ✓ ለሥራ ማመልከቻ ደብዳቤ
- ✓ የተፈጥሮ ሐብትን መጠበቅ
- ✓ የጉዞ ማስተወሻ
- ✓ የጊዜ አጠቃቀም

# አባሪ ሁለት፤ የፈተና ውጤት

| የሙከራ ቡድን | | | የቁጥጥር ቡድን | | |
|---|---|---|---|---|---|
| መ.ከ | ቅድመ ፈተና | ድህረ ፈተና | መ.ከ | ቅድመ ፈተና | ድህረ ፈተና |
| 1 | 46 | 58 | 1 | 53 | 43 |
| 2 | 33 | 65 | 2 | 21 | 50 |
| 3 | 41 | 46 | 3 | 43 | 29 |
| 4 | 48 | 59 | 4 | 28 | 44 |
| 5 | 62 | 73 | 5 | 49 | 59 |
| 6 | 38 | 57 | 6 | 32 | 37 |
| 7 | 53 | 67 | 7 | 30 | 51 |
| 8 | 50 | 55 | 8 | 39 | 43 |
| 9 | 45 | 59 | 9 | 33 | 45 |
| 10 | 63 | 76 | 10 | 63 | 45 |
| 11 | 31 | 51 | 11 | 33 | 37 |
| 12 | 50 | 65 | 12 | 52 | 52 |
| 13 | 48 | 59 | 13 | 46 | 47 |
| 14 | 47 | 54 | 14 | 45 | 48 |
| 15 | 40 | 50 | 15 | 41 | 37 |
| 16 | 52 | 60 | 16 | 47 | 50 |
| 17 | 41 | 34 | 17 | 43 | 31 |
| 18 | 55 | 65 | 18 | 55 | 54 |
| 19 | 47 | 50 | 19 | 47 | 40 |
| 20 | 45 | 57 | 20 | 45 | 45 |
| 21 | 50 | 62 | 21 | 52 | 49 |
| 22 | 55 | 52 | 22 | 48 | 27 |
| 23 | 41 | 59 | 23 | 42 | 42 |
| 24 | 61 | 73 | 24 | 61 | 59 |
| 25 | 31 | 43 | 25 | 30 | 48 |
| 26 | 46 | 61 | 26 | 47 | 48 |
| 27 | 34 | 56 | 27 | 34 | 40 |
| 28 | 19 | 32 | 28 | 24 | 11 |
| 29 | 41 | 58 | 29 | 43 | 54 |
| 30 | 27 | 44 | 30 | 29 | 27 |
| 31 | 44 | 58 | 31 | 45 | 51 |
| 32 | 46 | 63 | 32 | 47 | 49 |
| 33 | 59 | 26 | 33 | 16 | 26 |
| 34 | 31 | 43 | 34 | 50 | 40 |
| 35 | 51 | 60 | 35 | 40 | 57 |